

THE HSC HEALTH CARE SYSTEM

Health Services for Children with Special Needs, Inc.

*Caring. Serving. Empowering.*



# የተመዝጋቢ መመሪያ መጽሐፍ



ለበለጠ መረጃ፣
visit: www.hscsnhealthplan.org
ምክንያታዊ ለሆኑ
አቅርቦቶች፣ እባክዎ ይደውሉ
(202) 467-2737


1101 Vermont Avenue, NW | 12th Floor | Washington, DC 20005
1 (866) WE-R-4-KIZ (937-4549) – ከክፍያ ነጻ



ኦክቶበር 2021

THE HSC HEALTH CARE SYSTEM

# Health Services for Children with Special Needs, Inc.

በቀን ለ24 ሰዓታት በሳምንት ለ 7 ቀናት ሊደውሉልን ይችላሉ። የቢሮ የሥራ ሰዓታችን ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጠዋቱ 8:00 እስከ ምሽት 5:30 ነው። ሁለት ስፍራዎች አሉን፣ ከታች ተዘርዝሯል። ከስፍራዎቹ አንዱን ለመጎብኘት፣ እባክዎ የደንበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶችን በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ያግኙ፣ ለ

አቅጣጫዎች ወይም ተጨማሪ መረጃ። በአካል ወይም ቨርችዋል (በኢንተርኔት) ለመገናኘት ቀን እና ሰዓትን ቀጠሮ ለመያዝ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎ ለእንክብካቤ አስተዳዳሪዎ ይደውሉ።

**ልዩ ፍላጎቶች ላላቸው ልጆች የጤና አገልግሎቶች፣ Inc. (HSCSN)**
**1101 Vermont Avenue NW, 12th Floor**
**Washington, D.C. 20005**
በጣም ቅርብ የሆነው ሜትሮ ጣቢያ ማክፌርሰን አደባባይ ነው፣
ከኛ ቢሮ 3 ረድፍ ነው።

**HSCSN Wellness Center**
**3400 Martin Luther King Jr. Avenue SE**
**Washington, D.C. 20032**
በጣም ቅርብ የሆነው ሜትሮ ጣቢያ የኮንግሬስ ሃይትስ ነው፣
ከቢሮአችን 1 ብሎክ ላይ ይገኛል።

## ENGLISH

If you do not speak and/or read English, please call (202) 467-2737.
A representative will assist you.

## SPANISH

Si no habla ni lee inglés, llame al (202) 467-2737. Un representante lo asistirá.

## VIETNAMESE

Nếu quý vị không nói và/hoặc đọc Tiếng Anh, vui lòng gọi (202) 467-2737.
Một người đại diện sẽ hỗ trợ quý vị.'

## AMHARIC

እንግሊዘኛ መናገር/ወይም ማንበብ ካልቻሉ፣ እባክዎ በዚህ ስልክ ቁጥር (202) 467-2737.
ይደውሉ። ተወካይ ይረዳዎታል።

## KOREAN

영어를 구사하지 못하시거나 읽지 못하시는 경우, (202) 467-2737.
중에 연락해 주십시오. 상담원이 도움을 드릴 것입니다.

## FRENCH

Si vous ne parlez pas et / ou ne lisez pas l'anglais, appelez le (202) 467-2737.
Un représentant vous aidera.

## ARABIC

إذا كنت لا تتحدث و/أو تقرأ الإنجليزية، فيرجي الاتصال برقم 467-2737 (202) أحد الممثلين.

## MANDARIN

如果您不会说和/或读英语，请致电(202) 467-2737。我们的服务代表将为您提供协助。

## RUSSIAN

Если вы не говорите и / или не читаете по-английски, звоните по телефону
(202) 467-2737. Представитель поможет вам.

## BURMESE

သငျသညျအင်္ဂလိပ်စကားပြောနှင့် / သို့မဟုတ်စာမဖတ်ကြဘူးဆိုရင်, (202) 467-2737.
ကိုခေါ်ပါ။ တစ်ဦးကကိုယ်စားလှယ်သင်ကူညီကြလိမ့်မည်.

## CANTONESE

如果您不會說和/或讀英語，請致電 (202) 467-2737。我們的服務代表將為您提供協助。

## FARSI

اگر انگلیسی صحبت نمی کنید/نمی خوانید، لطفا بین ساعات (202) 467-2737.
با شمارهتماس بگیرید .یکی ازنمایندگان ما به شما کمک خواهد کرد.

## POLISH

Osoby, które nie potrafią mówić lub czytać po angielsku, mogą zadzwonić na numer (202) 467-2737.
aby skorzystać z pomocy konsultanta.

## PORTUGUESE

Caso você não fale/leia em inglês, ligue para (202) 467-2737. Um representante o ajudará.

## PUNJABI

ਜੇਕਰ ਤੁਸੀਂ ਅੰਗਰੇਜ਼ੀ ਬੋਲਦੇ ਅਤੇ/ਜ ◌ਾ◌ਂ ਪੜ੍ਹਦੇ ਨਹੀਂ, ਕਕਰਪ ਕਰਕੇ ਦੇ ਕਿਚਕ ਰ (202) 467-2737
ਉੱਤੇ ਕ ਲ ਕਰੋ। ਇੱਕ ਪਰਤ਼ੀਕਨਧ ਤੁਹ ਡ਼ੀ ਸਹ ਇਤ ਕਰੇਗ ।

## HAITIAN CREOLE

Si ou pa pale ak/oswa li Angle, tanpri rele (202) 467-2737. Yon reprezantan ap ede w.

## HINDI

यदि आप अंग्रेज़ी बोलते और/या पढ़ते नहीं, कृपया 8 a.m.-6 p.m. के बीच (202) 467-2737
पर कॉल करें। एक प्रतिनिध आपकी सहायता करेगा।

## SOMALI

Haddii aadan ku hadlin iyo/ama qorin luuqada Ingiriiska, fadlan wac lambarkan (202) 467-2737.
wakiil ayaa ku caawin doona.

## HMONG

Yog tias koj tsis hais thiab/lossis nyeem tau Lus As Kiv, thov hu rau (202) 467-2737.
Ib tug neeg sawv cev yuav pab tau koj.

## ITALIAN

Se ha difficoltà a parlare e/o leggere la lingua inglese, chiami il numero (202) 467-2737.
Un rappresentante le presterà assistenza.

## TAGALOG

Kung hindi ka nakakapagsalita at/o nakakapagbasa ng Ingles, pakitawagan ang (202) 467-2737. May kinatawan na tutulong sa iyo.

## JAPANESE

（202）467-2737 までお電話ください。担当者があなたをサポートします。

# አስፈላጊ የስልክ ቁጥሮች

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ለጥያቄዎች ስለ HSCSN፣** | የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች | (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| | TTY/TDD የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች | (202) 467-2709 | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| **የሀኪምዎ ቢሮ ከተዘጋ በኋላ እንክብካቤ ከፈለጉ፥** | የነርስ የስልክ መስመር | (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| | TTY/TDD የነርስ የስልክ መስመር | (202) 467-2709 | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| **በ24 ሰዓታት ውስጥ ሀኪም ጋር መታየት ካስፈለገዎ (አስቸኳይ ህክምና)፣** | የእርስዎ **PCP** ቢሮ | (የእርስዎን **PCP** መረጃ እዚህ ይሞሉ) | |
| | የነርስ የስልክ መስመር | (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 | 24 ሰዓታት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት |
| **ወደ ቀጠሮዎ የሚያደርስዎ መጓጓዣ ከፈለጉ፣** | Southeastern (SET) | 1-866-991-5433 | |
| | የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች | (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 | |
| **የአይምሮ ጤና እንክብካቤ ካስፈለገዎ ወይም ስለ አእምሮ ጤና ጥያቄ ካሎት፣** | የእርስዎ **PCP** ቢሮ | (የእርስዎን **PCP** መረጃ እዚህ ይሞሉ) | |
| | የነርስ የስልክ መስመር | (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| | የዲሲ የባህርይ ጤና መምሪያ ማግኛ ዲፓርትመንት የእርዳታ የጥሪ መስመር | 1-(888) 793-4357 | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| **እርስዎ የሚናገሩትን ቋንቋ የሚናገር ሰው ከፈለጉ ወይም መስማት የተሳንዎት ከሆነ፣** | የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች | (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| | TTY/TDD የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች | (202) 467-2709 | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| **የጥርስ ህክምና ጥያቄዎች፣** | ዴልታ የጥርስ ህክምና የደምበኛ አገልግሎት | 1 (888) 258-8023 | ጧት 8 እስከ ምሽት 8 ከሰኞ እስከ ዓርብ |
| **የዓይን ህክምና ጥያቄዎች፣** | የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች | (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| **ለድንገተኛ አገልግሎት፣ ወደ 911 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚያገኙት የድንገተኛ ክፍል ይሂዱ።** | | | |

# የግል መረጃ

የእኔ My Medicaid መታወቂያ ቁጥር፥

የእኔ ዋና ህክምና አቅራቢ (PCP)፥

የእኔ ዋና ህክምና አቅራቢ (PCP) አድራሻ፥

የእኔ ዋና ህክምና አቅራቢ (PCP) ስልክ ቁጥር፥

የልጅ Medicaid መታወቂያ ቁጥር፥

የልጅ/ልጆች ዋና ህክምና አቅራቢ (PCP)፥

የልጅ/ልጆች ዋና ህክምና አቅራቢ (PCP) አድራሻ፥

የልጅ/ልጆች ዋና ህክምና አቅራቢ (PCP) ስልክ፥

የኔ ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP)፣

የኔ ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP) አድራሻ፣

የኔ ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP) የስልክ ቁጥር፣

የልጅ/ልጆች ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP)፥

የልጅ/ልጆች ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP) አድራሻ፥

የልጅ/ልጆች ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP) ስልክ፥

# ማውጫ ሠንጠረዥ

**አስፈላጊ የስልክ ቁጥሮች** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . **4**

**የግል መረጃ** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . **5**

**ማውጫ ሠንጠረዥ** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . **6**

**እንኳን ወደ HSCSN በሰላም መጡ** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10

ይህ የመመሪያ መጽሐፍ እንዴት እንደሚያገለግል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10

ይህ መመሪያ መጽሃፍ እንዴት እንደሚረዳዎት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10

**የእርስዎ መብቶች።** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . **11**

**የእርስዎ ሃላፊነቶች** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . **12**

**የእርስዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ቁጥር** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . **13**

የተመዝጋቢ መታወቂያዎ ይሄንን ይመስላል፡ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 13

**የእርስዎ ዋና የጤና ክብካቤ አቅራቢ (PCP)** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . **14**

የእርስዎን PCP መምረጥ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 14

የእርስዎን PCP መቀየር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 15

**የእርስዎ ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP)** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . **16**

የእርስዎን PDP መምረጥ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 16

የእርስዎን PDP መቀየር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 16

**መደበኛ እንክብካቤ፣ አስቸኳይ እንክብካቤ እና ድንገተኛ እንክብካቤ** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . **17**

መደበኛ እንክብካቤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 17

አስቸኳይ እንክብካቤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 17

ድንገተኛ ህክምና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 17

**ከከተማ ውጪ በሆኑ ጊዜ የሚሰጥ እንክብካቤ** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . **19**

ከከተማ ውጪ ሲሆኑ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 19

መደበኛ እንክብካቤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 19

አስቸኳይ እንክብካቤ . . . 19
ለድንገተኛ ህክምና . . . 19
**በኔትወርክ እና ከኔትወርክ ውጪ ያሉ አገልግሎት ሰጪዎች . . . 20**
**ቀጠሮ ማስያዝ . . . 21**
ከእርስዎ PCP ጋር ቀጠሮ መያዝ . . . 21
ቀጠሮን መቀየር ወይም መሰረዝ . . . 21
የእርስዎ PCP ወይም PDP ቢሮ ዝግ በሆነ ጊዜ እንክብካቤ ስለማግኘት . . . 21
**ሀኪምዎን ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ ይፈጅብዎታል? . . . 22**
**የድጋፍ አገልግሎቶች . . . 23**
የትራንስፖርት አገልግሎት . . . 23
የቤተሰብ ቴራፒ እና የጉዞ አገልግሎቶች . . . 24
የአስተርጓሚ እና የትርጉም አገልግሎቶች/የድጋፍ አገልግሎቶች መስማት እና ማየት ለተሳናቸው . . . 24
የአስተርጓሚ አገልግሎቶች . . . 24
የትርጉም አገልግሎቶች . . . 25
ተጨማሪ የድጋፍ አገልግሎቶች መስማት እና ማየት ለተሳናቸው . . . 25
**የስፔሺያሊቲ እንክብካቤ እና ሪፈራሎች . . . 26**
የስፔሺያሊቲ እንክብካቤ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል . . . 26
ራስን ሪፈር የማድረግ (Self-Referral) አገልግሎቶች . . . 26
የሚከተሉትን ለማድረግ ሪፈራል አያስፈልጎትም፥ . . . 26
**የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች . . . 27**
ለመጠጥ ወይም ሌላ አደንዛዥ ዕጽ መጠቀም አገልግሎቶች . . . 27
የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶች . . . 27
የኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ፣ የማማከር አገልግሎት እና ህክምና . . . 28

**የመድሃኒት ቤት አገልግሎት እና የሃኪም ትዕዛዝ የሚያስፈልጋቸው መድሃኒቶች ....... 29**

**የበሽታ አስተዳደር ....... 30**

**የእንክብካቤ ማስተባበር እና የእንክብካቤ አስተዳደር ፕሮግራሞች ....... 31**

**የእንክብካቤ አስተዳደር ፕሮግራም መብቶች እና ግዴታዎች ....... 33**

**ወጣት አዋቂዎች ከመታመም የሚከለክሉ አገልግሎቶች ....... 36**

የመከላከል የምክር አገልግሎት ....... 36

የአዋቂዎች ክትባት ....... 36

**እርግዝና ....... 37**

የቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ እንክብካቤ ....... 37

**የልጅዎ ጤና ....... 38**

Health Check ፕሮግራም ለህጻናት(EPSDT) ....... 38

ኢምግራንት ልጆች ....... 38

ለልጅዎ የጥርስ ህክምና ....... 38

ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎት ያላቸው ህጻናት ....... 39

የ IDEA ፕሮግራም ....... 39

ክትባቶች (በመርፌ የሚሰጡ) ለህጻናትና ለወጣቶች ....... 40

HSCSN የደህንነት የስጦታ ካርድ ፕሮግራም ....... 49

**Health Check ፕሮግራም ለህጻናት(EPSDT) ....... 50**

ለህጻናት እና ታዳጊዎች የሚመከር ክትባት ወይም የመርፌ ክትባት ጊዜ ሰሌዳ ....... 51

**የጤና ጥቅሞችዎ ....... 53**

በ HSCSN የሚሸፈኑ የጤና አገልግሎቶች ....... 53

የማንከፍልባቸው አገልግሎቶች ....... 60

የእንክብካቤ ሽግግር ....... 61

**ሌሎች ማወቅ የሚያስፈልግዎ ነገሮች ....... 62**

አድራሻ ከቀየርኩ ምን ማድረግ አለብኝ . . . 62
ልጅ ከወለድኩ ምን ማድረግ አለብኝ . . . 62
ልጅ በጉዲፈቻ ከወሰድኩ ምን ማድረግ አለብኝ . . . 62
ከቤተሰቤ ውስጥ አንድ ሰው ከሞተ ምን መድረግ አለብኝ . . . 62
የእኔን MCO እንዴት መቀየር እንደምችል . . . 62
የሚከተሉትን ካደረጉ፣ ከእንግዲህ ወዲያ የጤና እንክብካቤን ከ HSCSN እንዲያገኙ አይፈቀድልዎትም፥ . . . 63
የ D.C. መንግስት የሚከተሉትን ካደረጉ እርስዎን ከ HSCSN ሊሰርዝዎ ይችላል፣ . . . 63
ሽፋን ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቢል ከቀረበልኝ ምን ማድረግ አለብኝ . . . 63
ሽፋን ለማይሰጣቸው አገልግሎቶች መክፈል . . . 63
**የቀደመ መመሪያ . . . 64**
ሌላ ኢንሹራንስ ካለኝ ማድረግ የሚገባኝ . . . 64
ለ Medicaid እና Medicare ለሁለቱም ብቁ ከሆንኩ ምን ማድረግ አለብኝ . . . 64
**ማጭበርበር . . . 65**
የሃኪም የክፍያ እቅድ መግለጫ . . . 65
**ቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች . . . 66**
ቅሬታዎች . . . 66
ይግባኞችና ፍትሃዊ ችሎቶች . . . 66
ይግባኞች . . . 67
የተፋጠነ (አስቸኳይ) ቅሬታዎች እና የይግባኝ መስማት ሂደት . . . 68
የግላዊነት ተግባራት ማስታወቂያ . . . 68
Medicare እና Medicaid ሁለቱም ያላቸው ተመዝጋቢዎች የHSCSN Medicare Part D ማስታወቂያ . . . 74
**የጤና ጥበቃ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ቢሮ እና ቢል ኦፍ ራይትስ . . . 75**
**ትርጉሞች . . . 76**

# እንኳን ወደ HSCSN በሰላም መጡ

**ልዩ ፍላጎቶች ላላቸው ልጆች የጤና አገልግሎቶች፣ Inc. እንኳን በደህና መጣችሁ (HSCSN)።** HSCSN የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ እና ወጣቶች የተጨማሪ ዋስትና ገቢ ፕሮግራም (CASSIP) ለህፃናት እና ወጣቶች የጤና እንክብካቤ እቅድ አቅራቢ ነው። CASSIP የሚያስተዳድረው የእርስዎ፣

- የሕክምና እንክብካቤ
- የጥርስ ህክምና
- የሥነ ባሕሪያዊ ጤና አገልግሎቶች
- ለአልኮል እና አደንዛዥ እጽ አላግባብ መጠቀም አገልግሎቶች
- የእይታ አገልግሎቶች

የ HSCSN የጤና እቅድ፣ ልዩ ፍላጎቶች ያላቸው እና ተጨማሪ የዋስትና ገቢ (SSI)ጥቅማጥቅሞችን ለሚያገኙ ወይም ለ SSI- ብቁ ለሆኑ ህፃናት እና ወጣት ሰዎች (ዕድሜ ከ 0 እስከ 26) ነው።

***ይህንን መመሪያ በጥንቃቄ እንዲያነቡ ያስፈልጋል። ሲፈልጉ እንዲያገኙት፣ ደህንነት ያለው በቀላሉ ሊያገኙት የሚችሉበት ቦታ ያስቀምጡ።***

## ይህ የመመሪያ መጽሐፍ እንዴት እንደሚያገለግል

HSCSN የጤና ጥበቃ እንዲያገኙ የሚረዳዎት ክፍያው በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሚሸፈን የእንክብካቤ እቅድ ነው። በዚህ የመመሪያ መጽሀፍ፣ HSCSN እንዴት እንደሚሰራ፣ ሐኪሞችን እንዴት እንደሚያገኙ፣ እንዴት እንደሚደውሉልን እና ክፍያ ስለምንፈጽምባቸው ነገሮች እንነግርዎታለን። በጤና እንክብካቤ ውስጥ እና በእርስዎ ሀኪም የሚነገሩ ቃላትን መረዳት አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪ ይሆናል። እርስዎን ለማገዝ፣ ከዚህ መፅሃፍ ጀርባ ትርጉሞች በሚለው ክፍል ላይ እነዚህን ቃላት አብራርተናል።

በዚህ መጽሀፍ ስለሚያነቧቸው ነገሮች ጥያቄዎች ካሎት ወይም ስለ HSCSN ሌሎች ጥያቄዎች የ HSCSN ደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 መደወል ወይም www.hscsnhealthplan.org መጎብኘት ይችላሉ እና እኛ እርስዎን ለመርዳት የተቻለንን እናደርጋለን።

## ይህ መመሪያ መጽሃፍ እንዴት እንደሚረዳዎ

ይሄ የአባል መመሪያ መጽሐፍ የሚነግርዎ፡

- የጤና እንክብካቤን እንዴት እንደሚያገኙ
- የእርስዎ የሚሸፈኑ አገልግሎቶች
- የማይሸፈኑ አገልግሎቶች
- ዋና የእንክብካቤ አቅራቢዎ (PCP) እና ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢዎን (PDP) እንዴት መምረጥ እንደሚችሉ።
- ከታመሙ ምን ማድረግ እንደሚገባዎት።
- ቅሬታ ካሎት ወይም HSCSN የሰጠውን ውሳኔ እንዴት ማስቀየር(ይግባኝ) ማለት እንደሚችሉ።

ይህ የተመዝጋቢ መመሪያ መጽሐፍ HSCSN እንዴት እንደሚሰራ መሰረታዊ መረጃን ይሰጥዎታል። ማንኛውም ጥያቄዎች ካሎት እባክዎ የ HSCSN የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በማንኛውም ጊዜ፣ በቀን 24 ሰዓታት፣ እና በሳምንት 7 ቀናት ይደውሉ።

# መብቶችዎ

- ከሃኪሞችዎ እና ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎችዎ ጋር ሲነጋገሩ በሚስጥር የሚያዝ መሆኑን ይወቁ።
- ህመም ወይም ህክምና እርስዎ በሚረዱት ቋንቋ እንዲብራራልዎ ማድረግ።
- ሕክምናውን ያለመቀበል መብትን ጨምሮ፣ የጤና እንክብካቤዎን በሚመለከት ውሳኔዎች ላይ መሳተፍ።
- መረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲሰጡ፣ የተሟላ፣ ግልጽ፣ እና የሚገባ የህክምና አማራጮችን እና የእያንዳንዱን አማራጭ አደጋዎችን የሚመለከት ማብራሪያ ማግኘት።
- ህክምናን ወይም እንክብካቤን አለመቀበል።
- ለማስገደድ፣ ዲስፕሊን፣ አመቺነት ወይም ብቀላ ከሚያገለግሉ ማንኛውም ዓይነት ክልከላዎች ወይም ማግለሎች ነፃ መሆን።
- የህክምና መዝገቦችዎን መመልከት እና ቅጂውን ማግኘት እና ትክክል ካልሆነ፣ ማሻሻያ ወይም ለውጥን መጠየቅ።
- ያሉትን እና ለእርስዎ ተደራሽ የሆኑ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን በጊዜው ማግኘት።
- የእርስዎን PCP/PDP በ HSCSN ኔትዎርክ ውስጥ ካሉ ብቁ አቅራቢዎች መምረጥ ወይም መቀየር።
- ያገኙት እንክብካቤ ላይ ቅሬታ ማቅረብ እና ምላሽ ማግኘት።
- HSCSN አገልግሎትን ወይም ዕቃን መከልከሉ፣ መቀነሱ ወይም ማቆሙ ትክክል አይደለም ብለው ካመኑ ይግባኝ ወይም ፍትሃዊ የክስ መስማት ሂደት መጠየቅ።
- ከመረጡት የአገልግሎት አቅራቢ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን እና ግብዓቶችን ማግኘት።
- ካለ አላስፈላጊ መጓተት የህክምና እንክብካቤ ማግኘት።
- በኔትወርክ ውስጥ ካለ ብቁ የጤና ጥበቃ ባለሞያ ሁለተኛ አስተያየት ማግኘት፣ ወይም፣ አስፈላጊ ሲሆን ለእርስዎ ያለምንም ወጪ ከኔትወርክ ውጪ ካለ ማግኘት።
- ስለ ቀደሙ መመሪያዎች መረጃ ማግኘት እና ማንኛውም ህይወት አድን ህክምናዎችን ላለማግኘት ወይም ላለመቀጠል መምረጥ።
- የ HSCSN የአባል መምሪያ መጽሃፍ እና/ወይም የአቅራቢ ማውጫ ቅጂ ማግኘት።
- አዲስ የህክመና ዕቅድ እስከሚኖርዎ ድረስ እያገኙ ያለውን ህክምና መቀጠል።
- ያለ ክፍያ የአስተርጓሚ እና የትርጉም አገልግሎቶችን ማግኘት።
- የቃል ማስተርጎም አገልግሎቶችን ማግኘትን አለመቀበል።
- ያለምንም ክፍያ የትራንስፖርት አገልግሎት ማግኘት።
- ስለ ቅድመ ፈቃድ ሂደቶች ገለጻ ማግኘት።
- ስለ HSCSN የፋይናንስ ሁኔታ እና ለሀኪሞቻችን ክፍያ ስለምንፈጽምበት ማንኛውም ልዩ ዘዴዎች መረጃ ማግኘት።
- የደምበኞች እርካታን በተመለከተ የተሰራ የዳሰሳ ጥናትን ማጠቃለያ ማግኘት።
- በትዕዛዝ ለሚሰጡ መድሃኒቶች የ HSCSN "ዲስፔንስ አስ ሪትን (እንደተጻፉ መድሃኒቶችን ይስጡ)" ፖሊሲን ማግኘት።
- የሁሉም የሚሸፈኑ መድሃኒቶች ዝርዝር ማግኘት።
- የእርስዎን ክብር እና የግላዊነት ባገናዘበ ሁኔታ በክብር መስተናገድ።
- በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ ማናቸውንም ጉልህ ለውጦች፣ ለውጡ ሥራ ላይ እንዲውል ከታቀደበት ጊዜ በ30 ቀናት ውስጥ ማስታወቂያውን ማግኘት።

# የእርስዎ ግዴታዎች

**እርስዎ የሚከተሉትን የማድረግ ግዴታ አለብዎ፣**

- የሚንከባከብዎትን ሰዎች ክብር እና ሰብዓዊነት መጠበቅ።
- የDC Medicaid ማኔጅድ የእንክብካቤ ፕሮግራም እና የ HSCSN ህጎችን መተግበር።
- ከሃኪሞችዎ እና ሌሎች አቅራቢዎች የሚሰጥዎትን መመሪያ መተግበር።
- በተያዙ ቀጠሮዎች መገኘት።
- ቀጠሮዎን መሰረዝ ካለብዎ ለሃኪምዎ ከቀጠሮው ቢያንስ ከ24 ሰዓት በፊት ማሳወቅ።
- የሃኪምዎን መመሪያ ካልተረዱ ተጨማሪ መረጃ መጠየቅ።
- ድንገተኛ ህመም ሲያጋጥምዎ ብቻ ወደ ድንገተኛ ህክምና ክፍል መሄድ።
- ጤናዎ ላይ ተጽዕኖ ያላቸውን የህክምና ወይም የግል ችግሮችን ለእርስዎ PCP ወይም PDP መንገር።
- እርስዎ ወይም የእርስዎ ቤተሰብ ሌላ የጤና መድን ካላቹ ወይም የአድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር ለውጥ ካላችሁ ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) እና HSCSN ሪፖርት ማድረግ።
- በቤተሰብ ዎ ውስጥ ለውጥ ካለ (ለምሳሌ፣ ሞት ወይም ልደት) ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) እና HSCSN ሪፖርት ማድረግ።
- የጤና ችግርዎን ለመረዳት መሞከር እና የህክምና ግቦችን ማዘጋጀት ላይ መሳተፍ።
- ከዚህ በፊት ሲታከሙባቸው ከነበሩ አቅራቢዎች ሀኪምዎ የእርስዎን የህክምና ሪከርድ እንዲያገኝ ማገዝ።
- በአደጋ ወይም በሥራ ላይ ጉዳት ከደረሰብዎ ለHSCSN መንገር።

# የእርስዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ቁጥር

ዋና የእንክብካቤ አቅራቢ (PCP) ከተመደበልዎ በኋላ፣ የተመዝጋቢ የመታወቂያ ካርድ በፖስታ እንልክልዎታለን። ይህ ካርድ እርስዎ የ HSCSN ተመዝጋቢ እንደሆኑ ለሀኪምዎችዎ፣ ሆስፒታሎችዎ፣ መድሃኒት ቤቶች፣ እና ሌሎች እንዲያውቁ የሚያደርግ ነው። እባክዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎ ላይ ያለው መረጃ ትክክለኛ መሆኑን ያረጋግጡ። ማንኛውም ችግር ካለ፣ ወይም ካርድዎ ከጠፋ፣ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ። እያንዳንዱ የ HSCSN ተመዝጋቢ፣ ልጆችን ጨምሮ፣ የራሱን ወይም የራሷን ካርድ አለው/አላት። የእርስዎን ካርድ(ዶች) ከእርስዎ ጋር ይያዙ፣ እና እንዳይጠፉ፣ በጥንቃቄ ይያዙ። የእርስዎን የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ማድረግ ከህግ ውጪ ነው።

## የተመዝጋቢ መታወቂያዎ ይሄንን ይመስላል፥

የእርስዎን የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ማድረግ ከህግ ውጪ ነው።

### የካርዱ የፊተኛው ገጽ

**ተመዝጋቢ፥** የመጀመሪያ ስም፣ የአባት ስም፣ የአያት ስም
**የአባል የመታወቂያ ቁጥር፣** XXXXXXXXXX
**Medicaid ቁጥር፥** 7XXXXXXXX

**PCP የመጀመሪያ ስም፣ የአያት ስም**
**PCP የቡድን ስም**
**PCP የስልክ ቁጥር**

**PDP የመጀመሪያ ስም፣ የአያት ስም**
**PDP የቡድን ስም**
**PDP የስልክ ቁጥር**

THE HSC HEALTH CARE SYSTEM
Health Services for Children with Special Needs, Inc.
**የተመዝጋቢ መታወቂያ ቁጥር**

**የጋራ ክፍያዎች - OV፤ $0** **RX፥$0** **ER፥ $0**

### የካርዱ የጀርባ ገጽ

ይህንን ካርድ ሁል ጊዜ ከእርስዎ ጋር ያዙ | የህክምና ድንገተኛ ሁኔታ እንዳለዎት ካሰቡ 911 ላይ ይደውሉ።

| | |
|---|---|
| **የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ 24 ሰዓታት/7ቀናት፥** | (202) 467-2737 |
| **LabCorp፥** | 1 (800) 762-4344 |
| **ቅድመ ፈቃድ (Prior authorization)፥ 24 ሰዓታት/7ቀናት፥** | (202) 467-2737 |
| **CVS ደምበኛ እንክብካቤ፥** | 1 (866) 885-4944፤ |
| **የዴልታ የጥርስ ህክምና ተቋም ኢንሹራንስ ኩባንያ፥** | 1(888) 258-8023 |
| **ሳውዚስትራንስ መጓጓዣ፥** | 1 (866) 991-5433 |
| **የባህሪያዊ ጤና መምሪያ፥** | 1(888) 793-4357 |
| **የኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA)፥** | (202) 645-4614 |

<u>የክፍያ ጥያቄዎች መቅረብ ይችላሉ ወደ፥</u>
HSCSN፣ ATTN፥ የክፍያ ጥያቄዎች መምሪያ፣ P.O. Box 29055, Washington, DC 20017. ይህ ካርድ ከተገኘ እባክዎ በደብዳቤ ይላኩ ወደ፥ HSCSN፣ Attn. የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ P.O. Box 29055, Washington, DC 20017
ለበለጠ መረጃ www.hscsnhealthplan.org ይጎብኙ።

ምክንያታዊ ለሆኑ አቅርቦቶች፣ እባክዎ ይደውሉ (202) 467-2737።

DHCF | GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR
ይህ ፕሮግራም ወጪው በከፊል የሚሸፈነው በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት የጤና ጥበቃ ፋይናንስ መምሪያ ነው።

*HSCSN አግባብነት ያላቸውን የፌዴራል ሲቪል ሕጎችን ያከብራል እና በዘር፣ ቀለም፣ የብሄራዊ ምንጭ፣ ዕድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት ወይም ጾታ መሰረት አድልዎ አያደርግም።*

**እባክዎ ሁልጊዜ የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን እና የፎቶ መታወቂያ ካርድዎን ይዘው መንቀሳቀስ ያስታውሱ። ሁልጊዜ ማንኛውም ህክምና ከማግኘትዎ በፊት ወይም መድሃኒት ከፋርማሲ ከመውሰድዎ በፊት መታወቂያ ካርድዎን ያሳዩ።**

# የእርስዎ ዋና የጤና እንክብካቤ አቅራቢ (PCP)

እርስዎ አሁን የ HSCSN ተመዝጋቢ እንደመሆንዎ መጠን፣ የእርስዎ ዋና እንክብካቤ አቅራቢ (PCP) የሚፈልጉትን የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ ይረዳዎታል።

እንክብካቤ ባስፈለገዎ ጊዜ መጀመሪያ ለPCPዎ መደወል አስፈላጊ ነው። እርስዎ HSCSN ጋር ከመመዝገብዎ በፊት PCP ከነበሮት፣ እባክዎ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549። እርስዎ ከዚያው PCP ጋር መቆየት የሚፈልጉ ከሆነ፣ እኛ ልናግዝዎ እንችላለን።

## የእርስዎን PCP መምረጥ

1. እርስዎ HSCSN በሚመዘገቡበት ጊዜ PCP ይምረጡ። እርስዎ የHSCSN ተመዝጋቢ ሆነው ባለበት ጊዜ ይህ ሰው የእርስዎ PCP ይሆናል።
    - የእርስዎ አሁን ያለው PCP የ HSCSN ኔትዎርክ አቅራቢ ከሆነ፣ ከዚያ ሀኪም ጋር መቆየት ይችላሉ።
    - PCP ከሌሎት፣ ከኛ የአገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ወይም ከ www.hscsnhealthplan.org ካሉት መካከል መምረጥ ይችላሉ።
    - ሀኪም ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጎት፣ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።
    - በእቅዳችን ውስጥ ከሆኑ ጀምሮ ባሉት የመጀመሪያ 10 ቀናት ውስጥ PCP ካልመረጡ፣ እኛ ለእርስዎ ሀኪም እንመርጥልዎታለን። እኛ የመረጥንልዎትን PCP ካልወደዱት፣ ሌላ PCP መቀየር ይችላሉ። የእርስዎን PCP ለመቀየር የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ(202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549።
    - HSCSN የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድን ይልክልዎታል። ካርድዎ የእርስዎን PCP ስምና ስልክ ቁጥር ይኖረዋል።
2. በእቅዳችን ውስጥ ላለው ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል፣ ልጆችን ጨምሮ፣ አንድ PCP ይምረጡ። የእርስዎ PCP ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፣
    - የቤተሰብ እና አጠቃላይ ሃኪም - ምአብዛኛውን ጊዜ አጠቃላይ ቤተሰቡን ማየት ይችላል።
    - የውስጥ ደዌ ሃኪም - አብዛኛውን ጊዜ አዋቂዎችን እና እድሜያቸው 14 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ አዋቂና ልጆችን ብቻ ያያሉ።
    - ፔዴትሪሺያን(የህጻናት ሀኪም) - አዲስ የተወለዱትን ህጻናትን ጨምሮ እስከ አዋቂ ልጆች ድረስ ያክማል።
    - የጽንስ/የማህጸን ሃኪም (OB/GYN) - የሴቶች ጤና እና የእናትነት ጤና ላይ ልዩ እውቀት ያለው።
    - እርስዎ ወይም ልጅዎ ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ካላችሁ፣ እርስዎ ስፔሺያሊስትን እንደርስዎ PCP ሊመርጡ ይችላሉ።
3. የእርስዎን PCP ሲመርጡ እባክዎ፥
    - ወደሚፈልጉት ሆስፒታል የሚልክዎ ሃኪም ለመምረጥ ይሞክሩ። ሁሉም ሃኪሞች ታካሚዎችን ወደ ሁሉም ሆስፒታሎች መላክ አይችሉም። የአገልግሎት አቅራቢዎቻችን ዝርዝሮች የእርስዎ PCP ወደ የትኛዎቹ ሆስፒታሎች መላክ እንደሚችሉ ያሳያሉ። በተጨማሪ ለእርዳታ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ።
    - አንዳንድ ጊዜ የመረጡት PCP አዲስ ታካሚዎችን ማየት አይችልም። ሌላ ሀኪም መምረጥ የሚያስፈልግዎ ከሆነ እናሳውቅዎታለን።
    - ለቤትዎ ወይም ለስራዎ የሚቀርብ ሃኪም ይምረጡ።

## የእርስዎን PCP እንዴት መቀየር ይችላሉ

የእርሶን PCP በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። ከአገልግሎት አቅራቢዎች መዝገብ ላይ አዲስ PCP መምረጥ ብቻ ነው የሚጠበቅብዎት። አዲሱን PCP ከመረጡ በኃላ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ (202) 467-2737 or 1 (866) 937-4549። አዲስ PCP ለመምረጥ እገዛ የሚሹ ከሆነ፣ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ሊያግዝዎ ይችላሉ።



# የእርስዎ ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP)

እርስዎ አሁን የ HSCSN ተመዝጋቢ እንደመሆንዎ መጠን፣ የእርስዎ PDP (ዋና የጥርስ ህክምና እንክብካቤ አቅራቢ) የሚፈልጉትን የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ ይረዳዎታል።

ዴልታ የጥርስ ህክምና ተቋምን ማግኘት ከፈለጉ፣ ለ HSCSN ደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 ይደውሉ። **ዴልታ የጥርስ ህክምና የደምበኞች አገልግሎት** በነፃ የስልክ መስመር 1 (888) 258-8023፣ ሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጧት 8:00 እስከ ምሽት 8:00 ኢስተርን ሰዓት አቆጣጠር ሊገኝ ይችላል። ድረገጻቸውን መጎብኘት ይችላሉ በ www.deltadentalins.com/hscsn።

እንክብካቤ ባስፈለገዎ ጊዜ መጀመሪያ ለPDPዎ መደወል አስፈላጊ ነው። እርስዎ HSCSN ጋር ከመመዝገብዎ በፊት የጥርስ ሀኪም ከነበሮት፣ እባክዎ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549። እርስዎ ከዚያው የጥርስ ሀኪም ጋር መቆየት የሚፈልጉ ከሆነ፣ እኛ ልናግዝዎ እንችላለን።

## የእርስዎን PDP መምረጥ

1. እርስዎ HSCSN በሚመዘገቡበት ጊዜ PDP ይምረጡ። እርስዎ የHSCSN ተመዝጋቢ ሆነው ባለበት ጊዜ ይህ ሰው የእርስዎ PDP ይሆናል።
    - የእርስዎ አሁን ያለው PDP የ HSCSN ኔትዎርክ አቅራቢ ከሆነ፣ ከዚያ የጥርስ ሀኪም ጋር መቆየት ይችላሉ።
    - PDP ከሌሎት፣ ከኛ የአገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ወይም ከ www.hscsnhealthplan.org ካሉት መካከል መምረጥ ይችላሉ።
    - የጥርስ ሀኪም ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጎት፣ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።
    - በእቅዳችን ውስጥ ከሆኑ ጀምሮ ባሉት የመጀመሪያ 10 ቀናት ውስጥ PDPን የማይመርጡ ከሆነ፣ ለእርስዎ የጥርስ ሃኪም እንመርጥልዎታለን። እኛ የመረጥንልዎትን PDP ካልወደዱት፣ የእርስዎን PDP መቀየር ይችላሉ። የእርስዎን PDP ለመቀየር የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ(202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549።
    - HSCSN የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድን ይልክልዎታል። ካርድዎ የእርስዎን PDP ስምና ስልክ ቁጥር ይኖረዋል።
    - በእቅዳችን ውስጥ ላለው ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል፣ ልጆችን ጨምሮ፣ አንድ PDP ይምረጡ። የእርስዎ PDP ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፣
        - የቤተሰብና አጠቃላይ የጥርስ ሃኪም - አብዛኛውን ጊዜ አጠቃላይ ቤተሰቡን ማየት ይችላል።
2. የእርስዎን PDP ሲመርጡ፣ እባክዎ፥
    - ወደሚፈልጉት ሆስፒታል የሚልክዎ  የጥርስ ሃኪም ለመምረጥ ይሞክሩ። ሁሉም ሃኪሞች ታካሚዎችን ወደ ሁሉም ሆስፒታሎች መላክ አይችሉም። የአገልግሎት አቅራቢዎቻችን ዝርዝሮች የእርስዎ PDP ወደ የትኛዎቹ ሆስፒታሎች መላክ እንደሚችሉ ያሳያሉ። በተጨማሪ ለእርዳታ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ።
    - አንዳንድ ጊዜ የመረጡት PDP አዲስ ታካሚዎችን ማየት አይችልም። ሌላ የ ጥርስ ሃኪም መምረጥ የሚያስፈልግዎ ከሆነ እናሳውቅዎታለን።

## የእርስዎን PDP እንዴት መቀየር ይችላሉ

የእርሰን PDP በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። ከአገልግሎት ሰጪዎች መዝገብ ላይ አዲስ PDP መምረጥ ብቻ ነው የሚጠበቅብዎት። አዲሱን PDP ከመረጡ በኃላ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ (202) 467-2737 or 1 (866) 937-4549። አዲስ PDP ለመምረጥ እገዛ የሚሹ ከሆነ፣ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ሊያግዝዎ ይችላሉ።

# መደበኛ እንክብካቤ፣ አስቸኳይ እንክብካቤ እና ድንገተኛ እንክብካቤ

እርስዎ ሊፈልጉ የሚችሉት ሶስት (3) ዓይነት የጤና እንክብካቤ አሉ፥ መደበኛ እንክብካቤ፣ አስቸኳይ እንክብካቤ፣ ወይም ድንገተኛ እንክብካቤ።

## መደበኛ እንክብካቤ

መደበኛ እንክብካቤ ከPCP በቋሚነት የሚያገኙት እንክብካቤ ነው። መደበኛ እንክብካቤ በተጨማሪ በእርስዎ PCP ከሚላኩ ሌሎች ሀኪሞች የሚያገኙት እንክብካቤን ያካትታል። መደበኛ እንክብካቤ ቼክአፕ፣ የአካል ምርመራ፣ የጤና ምርመራ፣ እና እንደ ስኳር፣ የደም ግፊት እና አስም ያሉ የጤና ችግሮችን መንከባከብን ያጠቃልላል። መደበኛ እንክብካቤ ማግኘት ከፈለጉ ወደ እርስዎ PCP ቢሮ በመደወል ቀጠሮ ማስያዝ ያስፈልግዎታል።

መደበኛ እንክብካበቤ ሊሆን የሚችለው፥

- ቼክአፖች/ምርመራዎች
- የደህንነት ጉብኝቶች
- የጤና ምርመራዎች
- እንደ ስኳር በሽታ፣ ደም ግፊት፣ እና አስም ያሉ የጤና ችግሮች እንክብካቤ።

## አስቸኳይ እንክብካቤ

የአስቸኳይ እንክብካቤ በ24 ሰዓታት ውስጥ ማግኘት ያለብዎ ነገር ግን አሁኑኑ መሆን የሌለበት የህክምና እንክብካቤ ዓይነት ነው። አስቸኳይ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው አንዳንድ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፥

- 101°F/38 ድግሪ ሴልሲየስ ትኩሳት።
- የጉሮሮ ሕመም
- ማስመለስ
- የጆሮ ህመም

**አስቸኳይ እንክብካቤ ካስፈለገዎ የእርስዎ PCP ቢሮ ጋር ይደውሉ።** የ PCP ቢሮ ዝግ ሲሆን፣ ስልኩን ያነሳው ሰው ጋር የስልክ መልዕክት ያስቀምጡ። ከዚያም በኃላ የነርስ የእርዳታ መስመር ቁጥር ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549. ይደውሉ። ነርሷ ወደ ሃኪም ባስቸኳይ  መሄድ እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ለመወሰን ትረዳዎታለች። በተጨማሪም ነርስ እንዴት እንክብካቤ ማግኘት እንዳለብዎ ይነግርዎታል። ለመደበኛ ወይም ለአስቸኳይ እንክብካቤ ድንገተኛ ክፍል መግባትም ሆነ አምቡላንስ መጠቀም የለብዎትም።

## ድንገተኛ እንክብካቤ

የድንገተኛ እንክብካቤ ለከባድ፣ ድንገተኛ ጉዳት (አንዳንድ ጊዜ ህይወት ላይ አደጋ የሚያመጣ) ጉዳት ወይም በሽታ የሚፈልጉት እንክብካቤ ነው። ለድንገተኛ ሁኔታ እንክብካቤ ማንኛውም ሆስፒታል የመጠቀም መብት አለዎት። ቅድመ-ማስፈቀጃ ለድንገተኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች አያስፈልግም።

ድንገተኛ ሁኔታ ያጋጠምዎት እንደሆነ—የባህርይ ጤና፣ የአልኮል መጠጥ፣ ወይም ሌሎች የአደንዛዥ ዕጽ ድንገተኛ ሁኔታን ጨምሮ—አቅራቢያዎ ወደሚገኝ ድንገተኛ ሕክምና መስጫ (ER) ወዲያውኑ ይሂዱ። ከከተማ ውጭ ሆነው እያለ ወደ ድንገተኛ ክፍል (ER) ከሄዱ፣ የክፍሉን ሰራተኛ የእርስዎ PCP ጋር እንዲደውል ይጠይቁ።

**ድንገተኛ ሁኔታ ካጋጠምዎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ**

1. **ወደ 9-1-1 መደወል ወይም አቅራቢያዎ ወደሚገኘው ድንገተኛ ክፍል መሄድ (ER)።**
2. **ለ ER የ HSCSN ተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን ያሳዩ።**
3. **በቻሉት ፍጥነት፣ የእርስዎ PCP ጋር ይደውሉ።**
4. **ከ ER ጉብኝትዎ በኋላ፣ እባክዎ የእርስዎን የHSCSN የጉዳይ አስተዳዳሪ ያግኙ።**



# ከከተማ ውጪ በሆኑ ጊዜ የሚሰጥ እንክብካቤ

## ከከተማ ውጪ በሆኑ ጊዜ

ከከተማ ውጪ እያሉ ሃኪም ጋር መታየት ወይም መድሃኒት ማግኘት ካለብዎ፤ የሚከተለውን ማድረግ አለብዎ፥

## መደበኛ እንክብካቤ

ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውጪ ያሉ ሃኪሞች የ HSCSN. አካል አይደሉም ስላልሆኑ፣ ከከተማ ውጪ ሲሆኑ አንድ ሃኪም ወይም አገልግሎት አቅራቢ ጋር ለመታየት ሲያስቡ ደውለው ለሚያገኙት ህክምና እንከፍል እንደሆነና እንዳልሆነ መጠየቅ አለብዎ። HSCSN ህክምናውን ከማግኘትዎ በፊት ፈቃደኝነቱን ካልገለጸልዎ፣ እራስዎ ለህክምናው መክፈል አለብዎ። ከከተማ ውጭ ሆነው እያለ መድሃኒት ካስፈለጎት፣ ከ CVS Health ጋር ኔትዎርክ ውስጥ ያለ ማንኛውንም መድሃኒት ቤት መጠቀም ይችላሉ። CVS Health ጋር በ 1 (866) 885-4944 ወይም HSCSN የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎት ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 በመደወል በኔትዎርክ ውስጥ ስላለ መድሃኒት ቤት ማወቅ ይችላሉ።

## አስቸኳይ እንክብካቤ

ለእርስዎ PCP ይደውሉ። የእርስዎ PCP ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ ለነርስ እርዳታ መስመር (የስልክ ቁጥር ያስገቡ #) ጋር ይደውሉ። ነርሷ ወደ ሃኪም ባስቸኳይ  መሄድ እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ለመወሰን ትረዳዎታለች። ነርሷ እንዴት እንክብካቤ ማግኘት እንዳለብዎ ትነግሮታለች። ለመደበኛ ወይም ለአስቸኳይ እንክብካቤ ድንገተኛ ክፍል መግባትም ሆነ አምቡላንስ መጠቀም የለብዎትም።

## ድንገተኛ እንክብካቤ

ድንገተኛ ሁኔታ ያጋጠምዎት እንደሆነ፣ የአዕምሮ ጤና፣ መጠጥ፣ ሌሎች የአደንዛዥ ዕጽ ድንገተኛ ሕመም ጨምሮ፣ ወዲያውኑ እንክብካቤ ለማግኘት ወደ አቅራቢያው የሚገኝ ድንገተኛ ሕክምና መስጫ (ER)ይሂዱ። ወደ ድንገተኛ ክፍል ከሄዱ የER ሰራተኛ ለእርስዎ PCP እንዲደውል መጠየቅ አለብዎ። ወደ ድንገተኛ
ክፍል ከሄዱ፣ በተቻለዎት ፍጥነት ለደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች መደወል አለብዎ። ቅድመ-ማስፈቀጃ ለድንገተኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች አያስፈልግም።

የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 በተቻለዎ ፍጥነት ይደውሉ። HSCSN ከኔትዎርካችን ውስጥም ሆነ ውጭ ላገኙት ድንገተኛ አገልግሎቶች ይከፍላል።

### ለሚሞሉ የትዕዛዝ መድሀኒቶች

ከከተማ ውጭ ሆነው እያለ የትዕዛዝ መድሃኒቶችን ለመሙላት ለ CVS ጤና ደምበኛ እንክብካቤ በ 1 (866) 885-4944 ይደውሉ።

ከከተማ ውጭ ሆነው እያለ ልጅዎ ሀኪም ማየት ካለበት፣ እባክዎ ለደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

# በኔትወርክ እና ከኔትወርክ ውጪ ያሉ አገልግሎት ሰጪዎች

**ከሀኪሞቻችን ወይም ሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎችን አንዳቸውን ሲጎበኙ፣ H**SCSN ለሚያገኙት እንክብካቤ ይከፍላል። እነዚህን ሃኪሞች እና የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች የኛ “ኔትወርክ” አገልግሎት ሰጪዎች እንላቸዋለን። እነዚህ ሁሉ በእኛ “ኔትወርክ ውስጥ ያሉ” ሃኪሞች የአገልግሎት ሰጪ መዝገብ ላይ ይገኛሉ። ሃኪም ወይም አገልግሎት ሰጪ የእኛ ካልሆነ “ከኔትወርክ ውጪ” አገልግሎት ሰጪ ይባላል።

“ከኔትወርክ ውጪ” ወደ ሆነ ሃኪም፣ ሆስፒታል ወይም ላብራቶሪ ከሄዱ ለሚያገኙት አገልግሎት እራስዎ መክፈል አለብዎ። እኛን መጀመሪያ ከጠየቁ እና እንደምንፈቅድ ከነገርኖት፣ አብዛኛውን ጊዜ በጽሁፍ አይከፍሉም። ይሄንን "ቅድመ ፈቃድ" **ብለን እንጠራዋለን።**

HSCSN ሽፋን ያለው አገልግሎት የሚሰጥ አቅራቢ በኔትወርክ ውስጥ ካሌለው፣ HSCSN ሽፋን ያላቸውን አገልግሎቶች ተቀባይነት ካለው ከኔትዎርክ ውጭ አቅራቢ (በበቂ እና በጊዜው) ይሰጣል።

እርስዎ ከአቅራቢ የክፍያ ደረሰኝ ከተቀበሉ፣ እባክዎ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

**አንዳንድ አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ በፊት ከ HSCSN ፈቃድ ያስፈልግዎታል።**
**ይህ ፈቃድ ቅድመ ፈቃድ (PA) ተብሎ ይታወቃል። ሁሉም ከኔትዎርክ ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ከድንገተኛ አገልግሎቶች ውጭ የቅድመ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል።**

ምንም እንኳን ከኔትዎርክ ውጭ ቢሆኑም የመረጡት የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት አቅራቢ ጋር መሄድ ይችላሉ። ቅድመ ፈቃድ አስፈላጊ አይደለም። ስለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት ገጽ 27ን ይመልከቱ።

# ቀጠሮ ማስያዝ

## ከእርስዎ PCP ጋር ቀጠሮ መያዝ

- የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን እና ወረቀት እና እርሳስ በቅርብ ይኑሮት።
- ወደ PCP ቢሮ ይደውሉ። በመታወቂያ ካርድዎ ፊት ለፊት ላይ የእርስዎን PCP ስልክ ይፈልጉ። በተጨማሪ በእርስዎ የአገልግሎት አቅራቢ የስልክ ማውጫ ወይም ኦንላይን በ www.hscsnhealthplan.org ሊያገኙት ይችላሉ።
- ስልኩን ለሚያነሳው ሰው እርስዎ የ HSCSN ተመዝጋቢ እንደሆኑ ይንገሩ። ከPCP ጋር ቀጠሮ መያዝ እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው።
- ላነሳ ሰው ቀጠሮውን ለምን እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው። ለምሳሌ፡
    - እርስዎ ወይም የቤተሰብ አባልዎ ህመም እየተሰማዎ መሆኑን
    - እራስዎን እንደጎዱ ወይም አደጋ እንደደረሰብዎት።
    - ቼክአፕ ወይም የክትትል እንክብካቤ እንደሚፈልጉ።
- የቀጠሮውን ሰዓት እና ቀን ይጻፉ።
- በጊዜ ወደ ቀጠሮዎ ይሂዱ፣ እና የእርስዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን እና ፎቶ ያለ መታወቂያዎን ይዘው ይምጡ።
- ቀጠሮ ለማስያዝ እርዳታ ከፈለጉ፣ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549.

## ቀጠሮን መቀየር ወይም መሰረዝ

- ወደ ቀጠሮዎ መሄድ እና በሰዓቱ መገኘት በጣም አስፈላጊ ነው።
- ቀጠሮዎን መቀየር ወይም መሰረዝ ከፈለጉ ፣እባክዎ ከቀጠሮው ሰዓት ቢያንስ ከ24 ሰዓት በፊት የሀኪም ቢሮው ጋር ይደውሉ።
- አንዳንድ ቀጠሮዎችን፣ ቀጠሮውን ለመሠረዝ ከቀጠሮው ከ 24 ሰዓታት በላይ በፊት አስቀድመው መደወል ይጠበቅብዎታል።
- ከቀጠሮው ከቀሩ ወይም ካረፈዱ፣ ሀኪምዎ የእርሱ ወይም የእርሷ ታካሚ እንዳይሆኑ መወሰን ይችላል።

## የእርስዎ PCP ወይም PDP ቢሮ ዝግ በሆነ ጊዜ እንክብካቤ ስለማግኘት

የእርስዎን PCP ወይም PDP ለማናገር ወይም ዋና የጥርስ ሃኪም ቢሮ ከተዘጋ፣ ወደ የእርስዎ PCP ወይም PDP ወይም ዋና የጥርስ ሃኪም ቢሮ ይደውሉ እና ስልኩን ለአነሳው ሰው መልዕክት ይተው ከነ ስልክ ቁጥርዎ። በተቻለ ፍጥነት አንድ ሰው መልሶ ይደውልሎታል። በተጨማሪ የነርስ ጥሪ መስመሩን በቀን 24 ሰዓታት መደወል ይችላሉ በ፣ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549። ድንገተኛ ሁኔታ እንዳጋጠሞት ካሰቡ፣ ወደ 911 ይደውሉ ወይም ወደ ድንገተኛ ክፍል ይሂዱ።

# ሀኪምዎን ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ ይፈጅብዎታል?

የሀኪምዎ ቢሮ በደወሉ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ቀጠሮ መስጠት አለበት። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ ቀጠሮ ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ያሳያል። በተጠቀሱት ጊዜዎች ውስጥ ቀጠሮ ማግኘት ካልቻሉ እባክዎ በ 202 ወይም 467-2737 ይደውሉ።

| የጉብኝት ዓይነት | የእርስዎ ሁኔታ | ሀኪምዎን ለማግነት ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ |
|---|---|---|
| **አስቸኳይ ጉብኝት** | ታመው ወይም ተጎድተው ሁኔታዎች እንዳይባባሱ በ24 ሰዓት ውስጥ ህክምና ማግኘት ሲኖርብዎ፣ ነገር ግን ወዲያውኑ ሃኪም ማየት አስፈላጊ ሳይሆን። የአስቸኳይ እንክብካቤ ጉዳዮች ምሳሌዎች፥<br>• 101°F/38 ድግሪ ሴልሲየስ ትኩሳት።<br>• የጉሮሮ ሕመም<br>• ማስመለስ<br>• የጆሮ ህመም | በ 24 ሰዓታት ውስጥ |
| **መደበኛ ህክምና** | መለስተኛ ህመም ወይም ጉዳት ሲኖርብዎ ወይም መደበኛ ምርመራ ማድረግ ሲኖርብዎ፣ ሆኖም ግን አስቸኳይ ቀጠሮ አያስፈልግዎትም። | በ 30 ቀናት ውስጥ |
| **ለክትትል ጉብኝት** | አንድ ጊዜ ከታከሙ በኋላ በደንብ እየተሻሎት መሆኑን ለማረጋገጥ ሃኪምዎን ማየት ያስፈልግዎታል። | እንደ ህክምናው ዓይነት ላይ ተመርኩዞ ከ1-2 ሳምንት ባለ ጊዜ ውስጥ |
| **የአዋቂዎች የደህንነት ጉብኝት** | • ከአዲስ ሃኪም ጋር የመጀመሪያ ቀጠሮዎን ሲይዙ።<br>• መደበኛ የአዋቂ ምርመራ ጊዜዎ ሲደርስ<br>• የፕሮስቴት ምርመራ፣ የፔልቪክ ምርመራ፣ የቅድመ ካንሰር ምርመራ (Pap smear) ወይም የጡት ምርመራ ጊዜዎ ሲደርስ | በ30 ቀናት ውስጥ ወይም አስፈላጊ ከሆነ ከዚያ አስቀድሞ |
| **ከስፔሺያሊስቶች ጋር አስቸኳይ ያልሆኑ ቀጠሮዎች (በሪፈራል)** | የእርስዎ PCP አስቸኳይ ላልሆነ ሁኔታ ስፔሺያሊስት ጋር እንዲሄዱ ሪፈር አድርገዎታል። | በ 30 ቀናት ውስጥ |
| **የልጅ EPSDT ምርመራዎች አስቸኳይ ያልሆነ** | ልጅዎ ለEPSDT ምርመራ ጊዜው ደርሷል | የመጀመሪያ ምርመራ፣<br>በ 60 ቀናት ውስጥ<br><br>ተጨማሪ ምርመራዎች፥ እድሜያቸው ከ ሁለት ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት ከቀጠሮው ጊዜ ጀምሮ በ 30 ቀናት ውስጥ፤ እድሜያቸው 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ልጆች ከቀጠሮ ቀን ጊዜ ጀምሮ በ 60 ቀናት ውስጥ |
| **IDEA (ቀደምት ጣልቃገብነት) ግምገማዎች** | የእድገት መዘግየት ወይም የአካል ጉዳተኝነት ስጋት ላላባቸው እድሜያቸው እስከ 3 ዓመት ልጆች ምርመራዎች ("ግምገማዎች")። | በ 30 ቀናት ውስጥ |

# የድጋፍ አገልግሎቶች

## የትራንስፖርት አገልግሎቶች

HSCSN የሚያስፈልግዎ ከሆነ ወደ ሀኪም ቀጠሮዎችዎ ትራንስፖርት ይሰጥዎታል። በተጨማሪ HSCSN ሽፋን ለሌላቸው አብዛኛው አገልግሎቶች የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል። ያልተሸፈኑ አገልግሎቶች ማለት በHSCSN የማይሸፈኑ፣ ነገር ግን በጤና እንክብካቤ ፋይናንስ ዲፓርትመንት (DHCF) ወይም ሌሎች የዲስትሪክቱ ኤጀንሲዎች የሚሸፈኑ አገልግሎቶች ናቸው። Southeastrans (SET) ድንገተኛ ላልሆነ ህክምና ትራንስፖርት የሚሰጡ ፈቃድ ያላቸው፣ የተመዘገቡ፣ የሰለጠኑ እና መድን ያላቸው የትራንስፖርት አቅራቢዎች ኔትዎርክ ያቀርባል።

- የትኛው ጊዜ እና ቀን ላይ መነሳት እንደሚፈልጉ ለመንገር ወደ Southeastrans (SET) ይደውሉ በ 1 (866) 991-5433።
- ትራንስፖርት ለማግኘት ከቀጠሮዎ ቢያንስ 24 በፊት ቀድመው መደወል አለብዎ (ቅዳሜ እና እሁድ ሳይጨምር)። ወደ EPSDT ለመሄድ ወይም ለሌሎች መደበኛ ጉብኝቶች ትራንስፖርት ከፈለጉ፣ ትራንስፖርት ለመጠየቅ ከቀጠሮው ቀን በፊት መደወል ይችላሉ።
- በዚያኑ ቀን ለሚያዙ ማንኛውም አስቸኳይ ቀጠሮዎች ቢያንስ 3 ሰዓታት ቀድመው መደወል አለብዎ።
- SET ከማንኛዉም አስቸኳይ የህክምና ፍላጎቶች በፊት 3 ሰዓታት አስቀድመው ለሚደውሉ ተመዝጋቢዎች አማራጭ የትራንስፖርት ምርጫዎችን አያቀርብም።
- የሚያገኙት የትራንስፖርት አይነት የህክምና ፍላጎትዎ ላይ ይመሰረታል። እነሱ የሚከተሉትን ያካትታሉ፣ ነገር ግን በዚህ አይወሰኑም፣
  - ዊልቼይር-ምቹ የሆኑ ቫኖች።
  - የመንገደኛ ተሽከርካሪዎች
  - አምቡላንሶች (ድንገተኛ-ያልሆኑ)።
  - አግባብ ሲሆን የህዝብ የጋራ ትራንስፖርት አማራጮች።
- የሚፈልጉትን ማንኛውም ልዩ ማረፊያዎችን ለ SET ይስጡ፥
  - የሚጓዙ የሰዎች ቁጥር።
  - የመኪና መቀመጫዎች
  - የእንቅስቃሴ መሳሪያ
  - የህክምና መሳሪያ
- ለ SET የተመዝጋቢ መታወቂያዎን፣ የስልክ ቁጥር እና የሚነሱበትን አድራሻ ይስጡ። በተጨማሪም የሚሄዱበትን የህክምና ተቋም/ የጥርስ ህክምና ወይም የሃኪም ቢሮ ስም፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር ይንገሯቸው።
- HSCSN በሳይኪያትሪክ ኗሪዎች የህክምና ተቋም (PRTF) ወይም አስፈላጊ የሆነ የህክምና እንክብካቤ ውስጥ የሚኖር ልጅዎን የቤተሰብ ቴራፒ ለመከታተል የረጅም ርቅት (ከዲሲ ከ 50 ማይልስ በላይ)የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ይሰጣል። የረጅም ርቀት ጉዞዎችን ለማሰናዳት በተቻለ ፍጥነት የጉዳይ አስተዳዳሪዎን ያግኙ።
- HSCSN ለቤተሰቦች የቤተሰብ የቴራፒ የጉዞ አገልግሎቶችን ይሰጣል። የቤተሰብ ቴራፒ ማለት እርስዎ ወይም ልጅዎ በ PRTF ሆናችሁ የሚደረግ የህክምና አካል ነው።

## የቤተሰብ ቴራፒ እና የረጅም ርቀት አገልግሎቶች

HSCSN በሳይኪያትሪክ ፍሪዎች የህክምና ተቋም (PRTF) ወይም አስፈላጊ የሆነ የህክምና እንክብካቤ ውስጥ የሚኖር ልጅዎን የቤተሰብ ቴራፒ ለመከታተል የረጅም ርቀት ጉዞ (ከዲሲ ከ 50 ማይልስ በላይ) ይሰጣል። በ PRTF ያለው የቤተሰብ ቴራፒ በ HSCSN ሊጸድቅ የሚገባው የልጅዎ የህክምና እቅድ አካል መሆን አለበት። ለህክምና አስፈላጊ የሆነ የረጅም ርቀት ጉዞ በ HSCSN ሊጸድቅ የሚገባው የተመዝጋቢው የእንክብካቤ የተቀናጀ እቅድ አካል ሊሆን ይገባል። ጉዞ ለማቀናጀት ከያዙት ቀጠሮ ቢያንስ ሁለት ሳምንት በፊት የእርስዎን HSCSN የእንክብካቤ አስተዳዳሪ ማግኘት አለብዎ።

**የሚከተለው የቤተሰብ ቴራፒ እና የረጅም ርቀት የትራንስፖርት አገልግሎቶች በ HSCSN ይሸፈናል፣**

- ለተንከባካቢ እና አንድ ተጨማሪ ሰው ወደ PRTF ወይም የአቅራቢው ተቋም እና ሆቴል ለሚደረግ ጉዞ።
- ወደ እና ከኤርፖርቶች፣ የባቡር ጣቢያዎች፣ እና የባስ ጣቢያዎች ለሚደረግ ጉዞ።
- እስከ ሁለት ምሽቶች ድረስ አንድ የሆቴል ክፍል ለእርስዎ እና አንድ ተጨማሪ ሰው። ክፍሉ ሁለት ክፍሎች ወይም ሁለት ኩዊን አልጋዎች ሊኖረው ይችላል።
- ከልጅዎ ጋር የህክምናው አካል የሆነው የቴራፒ የእረፍት ጉዞ። የቴራፒ እረፍት በ PRTF ህክምና ሃኪም እና ቡድን መጽደቅ አለባቸው። የቴራፒ ጉዞ ከተቋሙ ከ25 ማይል በላይ ከሆነ፣ ከHSCSN ፈቃድ በተጨማሪ ማግኘት አለብዎ። ከጉዞዎ በፊት ጥያቄውን ለማቅረብ የእንክብካቤ አስተዳዳሪዎን ያነጋግሩ።

**HSCSN የሚከተሉትን አይሸፍንም፣**

- የኪራይ መኪኖች
- ምግብ፣ ጌም፣ ልብሶች ወይም የቀን ጎዞዎች።
- የLyft(ሊፍት) ወይም የታክሲ ጉዞዎች ከህክምና ተቋሙ ከ25 ማይልስ (አንድ ጉዞ) ወይም ከ 50 ማይልስ በላይ የደርሶ መልስ ጉዞ። HSCSN ለግል ጥቅምዎ የLyft (ሊፍት) ጉዞዎችን አይሸፍንም። የግል ጥቅም ማለት ከልጁ ቴራፒ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ነገር ነው ማለት ነው።
- ከ50 ማይል በላይ መጓዝ ከፈለጉ፣ የ HSCSN ፈቃድ ማግኘት አለብዎ። ጥያቄዎን ለማቅረብ የእንክብካቤ አስተዳዳሪዎን ያግኙ።

# የአስተርጓሚና የትርጉም አገልግሎቶች/የድጋፍ አገልግሎቶች መስማት እና ማየት ለተሳናቸው

## የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

HSCSN ሆስፒታሎች ውስጥ ጨምሮ፣ የቃል የትርጉም አገልግሎቶች ሲፈልጉ በነጻ ያቀርብልዎታል።

የቃል የትርጉም አገልግሎት ለማግኘት እባክዎ የደምበኛ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 or 1 (866) 937-4549 ይደውሉ። የቃል የትርጉም አገልግሎትን ከፈለጉ እባክዎ ከሃኪም ቀጠሮዎ በፊት ይደውሉልን።

የቃል የትርጉም አገልግሎቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጠው በስልክ ነው። አስተርጓሚው ከእርስዎ ጋር የሃኪምዎ ቢሮ አብረው እንዲገኙ የሚፈልጉ ከሆነ፣ በ 5 ቀናት ውስጥ ወይም ቢያንስ ከቀጠሮው 48 ሰዓት በፊት ሊያሳውቁን ይገባል።

የቃል የትርጉም አገልግሎቶችን ከፈለጉ፣ HSCSN ያቀርባል። ይህ የሚያካትተው እርስዎ ወይም ልጅዎ በሆስፒታል ካሉ ነው።

የትርጉም አገልግሎት ከፈለጉ ከቀጠሮዎ በፊት እባክዎ ለደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

## የትርጉም አገልግሎቶች

ከ HSCSN መረጃ ካገኙ እና ወደ ሌላ ቋንቋ እንዲተረጎም ከፈለጉ፣ እባክዎ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ

## ተጨማሪ የድጋፍ አገልግሎቶች መስማት እና ማየት ለተሳናቸው

የመስማት ችግር ያለብዎ ከሆነ፣ ለደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ TTY/TTD (202) 467-2709 ይደውሉ።

የማየት ችግር ካለብዎ፣ ለደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ 1 (866) 937-4549 ወይም (202) 467-2737 ይደውሉ። እኛ መረጃ በድምጽ ካሴት፣ በብሬል፣ ወይም በትልቅ ህትመት ልንሰጥዎ እንችላለን።

# የስፔሺያሊቲ እንክብካቤ እና ሪፈራሎች

## የስፔሺያሊቲ እንክብካቤ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል

የእርስዎ PCP አብዛኛውን የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችን ማስተናገድ ይችላል። በተጨማሪ ከሌሎች አቅራቢዎች እንክብካቤ ሊፈልጉ ይችላሉ።

HSCSN ከተለያዩ ብዙ አቅራቢዎች አገልግሎቶችን ያቀርባል። እነዚህ አቅራቢዎች ስፔሺያሊስቶች ይባላሉ ምክንያቱም ልዩ የህክምና ስልጠና ስላላቸው ነው።

የእርስዎ እንክብካቤ አስተዳዳሪ ስፔሺያሊስት ማየት እናዳለብዎ ለማረጋገጥ ከእርስዎ እና ከእርስዎ PCP ጋር ይሰራል።

የእርስዎ PCP የእንክብካቤ ቅንጅት እቅድዎ ውስጥ የሌሉ የስፔሺያሊስት አገልግሎቶችን ለእርስዎ ለመስጠት የ HSCSN ሪፈራል እና የማጽደቅ ሂደትን ይከተላል።

የ HSCSN ኔትዎርክ ውስጥ የሌለው ስፔሺያሊስት ማየት ከፈለጉ፣ ግን ፈቃድ ካላገኙ እና HSCSN ለጉብኝቱ እንደማይከፍል ከገለጸ፤ እርስዎ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

- በ HSCSN ኔትወርክ ውስጥ ካለ ሌላ ሀኪም ጋር ቀጠሮ ይያዙ እና ሌላ ሁለተኛ አስተያየት ያግኙ።
- ውሳኔያችን ላይ ይግባኝ ማለት(ስለ ይግባኝ ገፅ 67ን ይመልከቱ)
- የይግባኝ ሂደቱን ካከናወኑ በኋላ ፍትሃዊ ችሎት ይጠይቁ (ስለ ፍትሃዊ ችሎቶች ገጽ 66ን ይመልከቱ)።

## ራስን ሪፈር የማድረግ (Self-Referral) አገልግሎቶች

ከ PCP ቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት ሳያስፈልግዎ ማግኘት የሚችሏቸው የተወሰኑ አገልግሎቶች አሉ። እነዚህም አገልግሎቶች የራስ ሪፈራል አገልግሎቶች የሚባሉ ሲሆን ዝርዝራቸውም ከታች ተቀምጧል።

### የሚከተሉትን ለማድረግ ሪፈራል አያስፈልጎትም፦

- PCPዎን ለማየት
- ድንገተኛ ሁኔታ በገጠመዎ ጊዜ እንክብካቤ ለማግኘት።
- በኔትዎርክ ውስጥ ካለ የእርስዎ የጽንስ/የማህጸን ሐኪም መደበኛ ወይም የመከላከል አገልግሎቶችን ለማግኘት (ሴቶች ብቻ)።
- የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ማግኘት።
- በግብረ ሥጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች (STIs) አገልግሎቶች።
- ክትባት ለማግኘት (በመርፌ)።
- ለስፔሺያሊቲ አገልግሎቶች የክትትል እንክብካቤ ማግኘት።
- በኔትወርክ ውስጥ ያለ የአይን ሃኪም ለማየት።
- ልጅዎን በኔትወርክ ውስጥ በሚገኝ የጥርስ ሕክምና አቅራቢ ጋር ለመውሰድ።
- መጠጥ ወይም ሌሎች ሱሶች ምክንያት የአእምሮ ጤና ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት።

# የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች

የአእምሮ ጤና ህክምና ለህጻናት እና ለአዋቂዎች ለሁለቱም ነው። ይህ ህክምና ጭንቀት ወይም ፍርሃት ሲሰማዎ የሚረዳዎ ነው።

እርዳታ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ወይም ከቤተሰብዎ ውስጥ አንድ ሰው እገዛ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፣ ይደውሉ

- የ HSCSN የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549።
- የዲሲ ቢሄቪየራል ሀልዝ መምሪያ (DBH) የስልክ መስመር 1-888-793-4357 ላይ፣24 ሰዓታት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት።

## ለመጠጥ ወይም ሌላ አደንዛዥ ዕጽ መጠቀም አገልግሎቶች

ከአልኮልና ከሌሎች አደንዛዥ እጾች ጋር ለተገናኙ ችግሮች ለእርስዎ ጤናና በዙሪያዎ ላሉ ሰዎች ጤና አደገኛ ናቸው። እነዚህ ችግሮች ላይ እገዛ ከፈለጉ ወደ ሃኪም መሄድ አስፈላጊ ነው። HSCSN የዲቶክስፊኬሽን አገልግሎቶችን ለማመቻቸት እና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚያግዝ የተቀናጀ እንክብካቤ ያቀርባል። ለእነዚህ ችግሮች አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፣

- የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር መደወል በ (202) 467-2737፣ 1 (866) 937-4549, or TTY/TTD (202) 467-2709፣ 24 ሰዓት በቀን፣ እና 7 ቀናት በሳምንት።
- የቢሄቪየራል ሄልዝ መምሪያ (DBH)  አሰስመንት ኤንድ ሪፈራል ሴንተር(ARC) መመሪያ ጋር በቀጥታ በ (202) 727-8473. 202 ይደውሉ።
- ሁሉም የአዕምሮ ጤና፣ የአልኮል፣ እና የሱስ አገልግሎቶች በሚስጥር የተያዙ ናቸው።

## የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶች

የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶችን ለማግኘት ሪፈራል አያስፈልጎትም። ሁሉም የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች ሚስጥራዊ ናቸው።

እርስዎ ከመረጡት አገልግሎት ሰጪ የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ። እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት ሪፈራል አያስፈልጎትም። ለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ከእርስዎ PCP ሌላ ሃኪም ማየት ከፈለጉ፣ ለ PCP ያሳውቁ። ለእርስዎ PCP የተሻለ እንክብካቤ እንዲያደርግልዎ ይረዳዋል። ስለ ወሊድ ቁጥጥር ወይም ሌሎች የቤተሰብ አገልግሎቶች መረጃ ለማግኘት PCPዎን ያነጋግሩ ወይም ለ HSCSN ደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ 202(202) 467-2737, 1 (866) 937-4549 ወይም TTY/TTD (202) 467-2709 ይደውሉ።

**የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች የሚያጣቃልላቸው፡**

- የእርግዝና ምርመራ
- ለሴቶችና ለጥንዶች የማማከር አገልግሎት።
- መደበኛ እና ድንገተኛ የወሊድ ቁጥጥር አገልግሎት።
- የምክር አገልግሎት እና ክትባቶች
- የማህጽን ምርመራ (ፓፕ ስሚር)።
- በግብረስጋ ግኑኝነት ለሚተላለፉ ሁሉም በሽታዎች ምርመራ
- ለሁሉም በግብረስጋ ግኑኝነት የሚተላለፉ በሽታዎች ህክምና።
- የማምከን ሥርዓቶች (ዕድሜዎ ከ 21 ዓመት በላይ እና ሂደቱ ከመካሄዱ 30 ቀን በፊት አስቀድመው ፎርም መፈረም አለብዎ።)
- ኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ እና የምክር አገልግሎት።

**የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች የሚከተሉትን አያጠቃልሉም፥**

- መደበኛ የማህጸን ጥናቶች ወይም ህክምናዎች።
- ለማኮላሸት የሚደረግ የማህጸን ማስወጣት ሂደት
- በፈቃድ የተደረገ ማኮላሸትን መመለስ።
- የኤችአይቪ/ኤድስ ህክምና
- ማስወረድ

## የኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ፣ የማማከር አገልግሎት እና ህክምና

የኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ እና የምክር አገልግሎት ማግኘት የሚችሉት፡

- የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ሲኖርዎ።
- ከእርስዎ PCP
- ከኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ እና የማማከር አገልግሎት ማዕከል።

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራ እና የማማከር አገልግሎት የት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት የደምበኛ እንክብካቤ አገልግልቶች ጋር ይደውሉ በ (202) 467-2737, 1 (866) 937-4549፣ ወይም TTY/TTD (202) 467-2709. የኤችአይቪ/ኤድስ ህክምና ማግኘት ከፈለጉ የእርስዎ PCP እንክብካቤውን እንዲያገኙ ይረዳዎታል። ወይም የእንክብካቤ አስተዳዳሪዎ ጋር መደወል ይችላሉ። በተጨማሪ እርስዎ ወይም ዶክተርዎ ለHIV/AIDs የመጋለጥ እድልዎ ሰፊ እንደሆነ የሚያምኑ ከሆነ የቅድመ-ተጋላጭነት የመከላከያ መድሃኒት (PrEP) ማግኘት ይችላሉ።

# የመድሃኒት ቤት አገልግሎት እና የሃኪም ትዕዛዝ የሚያስፈልጋቸው መድሃኒቶች

የመድሃኒት ቤቶች መድሃኒትዎን ሄደው የሚወስዱበት ቦታዎች ናቸው። ሀኪምዎ የመድሃኒት ማዘዣ ከሰጣቹ፣ የ HSCSN ኔትወርክ ውስጥ ወዳሉ መድሃኒት ቤቶች መሄድ ይገባዎታል።

የ HSCSN ኔትወርክ ውስጥ ያሉ የሁሉም መድሃኒት ቤቶች ዝርዝርን የHSCSN አቅራቢዎ መዝገብ ውስጥ ወይም ኦንላይን በ www.hscsnhealthplan.org. ማግኘት ይችላሉ።

ለዕርዳታ ወይም የታተመ ስሪት፣ እባክዎ ለደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

ከከተማ ውጭ ከሆኑ እና የድንገተኛ ሁኔታ ካጋጠመዎት ወይም አስቸኳይ እንክብካቤ ከፈለጉ፣ የ **ከከተማ ውጭ ሲሆኑ የሚሰጥ እንክብካቤ** ክፍልን በ ገጽ 19 ላይ ይመልከቱ።

**የሃኪም ማዘዣ ለመውሰድ፥**

- HSCSN ኔትወርክ አባል የሆነ እና ለሥራዎ እና ቤትዎ ቅርብ የሆነ መድሃኒት ቤት ይምረጡ።
- በሀኪም የታዘዘ መድሐኒት ፈቃድ ሲኖርዎ፣ ወደ መድሃኒት ቤቱ ይሂዱ እና ለፋርማሲስቱ የሐኪም ትዕዛዝ ማዘዣውን እና የ HSCSN የተመዝጋቢ መታወቂያዎን ይስጡት።
- ዕርዳታ ከፈለጉ፣ እባክዎ ለደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737፣ 1 (866) 937-4549፣
- ወይም TTY/TTD (202) 467-2709 ይደውሉ።

**ማስታወስ ያለብዎ ነገሮች፡**

- ለመድሐኒቶቹ ክፍያ እንዲፈጽሙ አይጠየቁም። መድሃኒት ቤቱ ወይም የመድሃኒት መደብሩ እንዲከፍሉ ከጠየቅዎ፣ ለ HSCSN ደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ይደውሉ።
- አንዳንድ ጊዜ፣ ሀኪምዎ ለመድሃኒት ከ HSCSN የቅድመ ፈቃድን (PA) ማግኘት ሊኖርበት ይችላል። ሃኪምዎ የቅድመ ፈቃዱን እየጠበቀ ባሉበት ወቅት፣ መድሃኒቶችን የማግኘት መብት አለዎት፥
    - ለ 72 ሰዓታት ወይም
    - የሚወስዱት በቀን ከአንድ ጊዜ በታች ከሆነ ለአንድ ሙሉ ዙር መድሃት።

# በሽታን መቆጣጠር

በጣም ስር የሰደደ በሽታ ወይም እንደ አስም፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ ወይም የአዕምሮ በሽታ የመሳሰሉ ልዩ የጤና ሕክምና የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ በእኛ የጤና እንክብካቤ አስተዳደር ፕሮግራም ውስጥ እንዲታቀፉ ልናደርግዎ እንችል ይሆናል። የእርስዎ የHSCSN የእንክብካቤ አቅራቢ በሽታዎን እንዲያስታምሙ እና ጤናማ እንዲሆኑ የሚያስችልዎትን አገልግሎቶች እና መረጃ እንዲያገኙ ያግዝዎታል።

የ HSCSN የበሽታ መቆጣጠር ፕሮግራም የተፈጠረው፣ የራስዎን/የልጅዎን አጠቃላይ የጤንነት ግቦችዎን ለመደገፍ የኛ ተመዝጋቢዎች ከጤና ጋር የተያያዘ ልዩ ሁኔታ(ዎች) ላይ ጥራት ያለው የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ ለመርዳት ነው። HSCSN ሥር የሰደደ የጤና ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ከተመዝጋቢዎቻችን ጋር አብሮ ይሰራል።

የእኛ የበሽታ አስተዳደር ፕሮግራም የ HSCSN ነባር የእንክብካቤ አስተዳደር ፕሮግራም አካል ነው። ከእርስዎ ሥር የሰደደ ሁኔታ ጋር የተያያዘ የቅንጅት ስራ የሚሰራው በእርስዎ የHSSN እንክብካቤ አስተዳዳሪ ወይም ከእርስዎ የእንክብካቤ አስተዳዳሪ ጋር በሚሰሩ ነርስ ነው።

**የበሽታ አስተዳደር ምንን ያካትታል?**

- ከእርስዎ/የልጅዎ ሁኔታ ጋር የተያያዘ የጤና ግምገማዎች።
- ሥር በሰደደ የጤና ሁኔታ ላይ የጤና ትምህርት።
- የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት።
- የእንክብካቤ ሁኔታውን የተዘጋጁ መመሪያዎችን በመከተል ማከናወን።
- ከሁኔታው ጋር ግንኙነት ካለው የHSCSN የእንክብካቤ አስተዳዳሪ የአካል ወይም ቨርችዋል(በኢንተርኔት)ጉብኝቶች።
- ወደ ማህበረሰብ ግብዓቶች ሪፈራሎች።
- ሥር የሰደደ የጤና ሁኔታውን ለመቆጣጠር ከእርስዎ/ከልጅዎ ሀኪሞች ጋር አብሮ መሥራት።

**ስለ HSCSN የበሽታ አስተዳደር ፕሮግራም ጥያቄዎች ካሉት፣ የእርስዎን እንክብካቤ አስተዳዳሪ ያግኙ ወይም የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ 202-467-2727 ወይም (202) 467-2737 ይደውሉ።**

# የእንክብካቤ ማስተባበር እና የእንክብካቤ አስተዳደር ፕሮግራሞች

የHSCSN የእንክብካቤ አስተዳዳሪ ፍላጎቶችዎን መሰረት በማድረግ ይረዳዎታል። እርስዎ የሚፈልጉትን ሁሉም የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለማቀናጀት እሱ ወይም እሷ የእርስዎ አጋር ነው/ች። የእንክብካቤ አስተዳዳሪዎች ልዩ ፍላጎቶች ካላቸው ህጻናት እና ወጣት ጎልማሶች ጋር ለመስራት ትምህርት እና ልምድ አላቸው። የእንክብካቤ አስተዳዳሪ የጤና እቅድ ውስጥ ከተመዘገቡ የመጀመሪያ 5 ቀናት ውስጥ ያገኝዎታል። እሱ ወይም እሷ የእንክብካቤ ቅንጅት እቅድዎን ለመጀመር መረጃ ለማግኘት በአካል ያገኙዎታል። የእንክብካቤ አስተዳዳሪ ስለ የእርስዎ ወይም የልጅዎ የሚከተሉት ነገር ይጠይቃል፥

- የህክምና ሁኔታ
- መድሃኒቶች
- የትምህርት ቤት መረጃ
- የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች

የHSCSN የእንክብካቤ አስተዳዳሪ እርስዎን ወይም የእርስዎን ልጅ በሚከተለው መልኩ ያግዛሉ፣

- ወጪው የተሸፈነ አገልግሎት ማግኘት ላይ
- የሕክምና ቀጠሮ እና ምርመራዎችን ማቀናጀት።
- ትራንስፖርት ማመቻቸት
- ትክክለኛውን አገልግሎት ማግኘትዎን ለማረጋገጥ መንገዶችን መፈለግ።
- ለልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችዎ ላይ ግብአቶችን እንዲያገኙ ማገዝ እና/ወይም የእርስዎ እንክብካቤ አቀራቢዎች የእለት ተለት ውጥረቱን እንዲቆጣጠሩ ማገዝ።
- ከማህበረሰብ እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ጋር መገናኘት።
- ጥቅማጥቅሞችዎ ሲያበቁ ወደ ሌሎች ተንከባካቢዎች እንዲሸጋገሩ ማድረግ፤ እርስዎ የመረጡት ሌላ MCO፣ ወይም ወደ አስፈላጊ ከሆነ ወደ DC Medicaid ክፍያ-ለ-አገልግሎት ፕሮግራም መዛወር።
- አቅራቢዎ ወይም የልጅዎ አቅራቢዎች በእንክብካቤ ቅንጅት እቅድ ውስጥ እንክብካቤውን እንደሚሰጡ ማረጋገጥ።
- የልጅዎ ትምህርት ቤት፣ የዲስትሪክት ኤጀንሲዎች፣ እና ከኔትወርክ-ውጭ-ያሉ አቅራቢዎች አገልግሎቶችን በህክምና እቅድ እየሰጡ መሆናቸውን ያረጋግጣል።
- የእርስዎን ወይም የልጅዎን ሁኔታ እንዲረዱ እና እንዴት እንደሚቆጣጠሩ ያግዛል።
- እርስዎን ወይም ልጅዎን መርዳት ከሚችሉ ማህበረሰቡ ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር ያገናኝዎታል።
- በዓመቱ ውስጥ የሚከተሉትን ለማድረግ በአካል ማግኘት፣
  - ግምገማዎችን ለመጨረስ
  - ስለ እንክብካቤ ፍላጎቶችዎ ለመነጋገር።
  - ለእርስዎ ወይም ለልጅዎ ስለ እንክብካቤ ቅንጅት እቅድ ለመነጋገር።

እርስዎ ወይም ልጅዎ ስር የሰደደ በሽታ ወይም እንደ ስኳር፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ የአዕምሮ በሽታ፣ ወይም አስም የመሳሰሉ ልዩ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው በሽታዎች ካለባችሁ፣ HSCSN ለጤና የእንክብካቤ ፍላጎትዎ ተጨማሪ እገዛ የሚሰጥ ልዩ አገልግሎቶች እና ፕሮግራሞች ሊያቀርብልዎ ይቻላል። እርስዎ ወይም ልጅዎ በሽታውን እንዲያስታምሙ እና ጤናዎን እንዲያሻሽሉ የሚያግዙ አገልግሎቶችን እና መረጃን እንዲያገኙ የሚያግዙ የእንክብካቤ አስተዳዳሪ ይኖራችኋል።

የእንክብካቤ አስተዳዳሪዎ የእርስዎን ወይም የልጅዎ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ በዓመት አንድ ጊዜ ወይም ከዚህ በላይ፣ በአካል ያገኝዎታል። ስለ እንክብካቤ አስተዳዳሪዎ ማንኛውም ቅሬታዎች ካሉት፣ እባክዎ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

የእኛ ሠራተኛ የበለጠ መረጃ ያቀርብላችኋል። በተጨማሪ በአሁኑ ሰዓት ለየትኛው ፕሮግራሞች እንደተመዘገቡ ያሳውቆታል። በተጨማሪ ሪፈራል መጠየቅ ወይም ከፕሮግራሙ እንዲወገዱ መጠየቅ ይችላሉ።



# የእንክብካቤ አስተዳደር ፕሮግራም መብቶች እና ግዴታዎች

HSCSN የተመዝጋቢዎችን በእያንዳንዱ የእንክብካቤ ክፍል ውስጥ የመሳተፍ መብቶችን ይመለከታል። ተመዝጋቢዎች ፍላጎቶቻቸው ምን እንደሆኑ በማወቅ እና በሕክምና ውስጥ በመሳተፍ ውሳኔ የመወሰን መብታቸውን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ። ይህም ያገኙትን አገልግሎት እና አገልግሎቱን የሚሰጡትን እንዲገመግሙ ያስችላቸዋል።

**I የሚከተሉትን ማድረግ የተመዝጋቢው እና የቤተሰቡ መብት ነው፣**

A. በ HSCSN ሠራተኞች በእንክብካቤ እና በክብር መታከም።
B. ሚስጥራዊነት
C. ስለ HSCSN አገልግሎቶች፣ አቅራቢዎች እና መብቶች እና ግዴታዎች ዓመታዊ መረጃ ማግኘት።
D. በእንክብካቤው ላይ የሚሳተፉ የሁሉንም የጤና እንክብካቤ ሠራተኞች እና አቅራቢዎችን ስም የማወቅ።
E. ስለ ተመዝጋቢዎች መብቶች እና ግዴታዎች ሀሳባቸውን ማጋራት።
F. በአባልነት ወይም በጥቅማጥቅሞች ላይ ማናቸውም ለውጦች ከመደረጋቸው በፊት በየዓመቱ ወይም ከለውጡ 30 ቀናት በፊት በጽሁፍ እንዲያውቁ መደረግ።
G. በኔትወርክ ውስጥ ያሉ አቅራቢዎችን መምረጥ ወይም መቀየር ወይም ፍላጎታቸውን የሚያሟሉ የእንክብካቤ አስተዳዳሪ ለውጥ መጠየቅ።
H. የጤና ፍላጎታቸውን ማወቅ እና ህክምናው ከመሰጠቱ በፊት ለህክምናው መስማማት።
I. አገልግሎቶች ከመሰጠታቸው በፊት ፈቃድ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ማወቅ (ለድንገተኛ አገልግሎቶች ፈቃድ አያስፈልግም)።
J. ወደ 911 እንዴት እና መቼ መደወል እንዳለብዎ ማወቅ።
K. ያሉትን የድንገተኛ ህክምና ሁኔታዎች እና የክትትል ህክምና እና አገልግሎቶች ማወቅ።
L. ወጪው ወይም የጥቅማጥቅሙ ሽፋን ምንም ይሁን፣ ለሁኔታቸው ትክክለኛ ወይም በህክምና አስፈላጊ የሆኑ አማራጮች ላይ ግልጽ የሆነ ውይይት ማድረግ።
M. የተመዝጋቢው የጤና እንክብካቤ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት አካል መሆን። ለተመዝጋቢው ህክምና ከመሰጠቱ በፊ አዎ ወይም አይ የማለት መብት አሎት። ተመዝጋቢዎች ሁለተኛ የባለሞያ ሀሳብ የማግኘት እና ህክምናን ያለመቀበል መብት አላቸው።
N. በኔትዎርክ ውስጥ አቅራቢ ከሌለ ተመዝጋቢው ምንም ክፍያ ሳይከፍል ከኔትዎርክ ውጭ ከሆነ አቅራቢ ሁለተኛ የባለሞያ ሀሳብ እንዲያገኝ HSCSN እንዲያመቻች ማድረግ።
O. ወደ ሁሉም አስፈላጊ የህክምና ቀጠሮዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ማግኘት።
P. የHSCSN ፖሊሲዎች እርስዎ ውሳኔ መስጠት እንዲችሉ እንዲያግዝዎ በሚረዱት ቋንቋ መሰጠት አለበት።
Q. ስጋቶችዎን እና አቤቱታዎችዎን ለ HSCSN ሠራተኞች ማቅረብ እና ምላሽ በጊዜው ማግኘት።
R. ስጋቶችዎን ወይም አቤቱታዎችዎን የበቀል እርምጃ ይወሰድብኛል የሚል ፍርሃት ሳይኖርዎ በማንኛውም ጊዜ ለማቅረብ የጤና እንክብካቤ ፋይናንስ ዲፓርትመንት (DHCF) የእምባ ጠባቂን ያግኙ። ፍትሃዊ ችሎት ያግኙ ወይም አስፈላጊ ከሆነ ከHSCSN ወይም DHCF ሠራተኞች እርዳታ ያግኙ።

S. የመሞት አደጋ ካለ እና የራስዎን የህክምና አማራጮች መውሰድ የማይችሉበት ሁኔታ ሲኖር ምን እንዲደረግ እንደሚፈልጉ በመግለጽ እና ስለ ልጅዎ ወይም የወጣት አዋቂ እንክብካቤን በተመለከተ እርስዎ እድሜዎ 18 ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ የቀደመ መመሪያዎች ይኑሮት፤ ለተመዝጋቢዎች የስቴት ህግ ላው ለውጥ ካለ ለወጡ ከተፈጠረበት ቀን ጀምሮ ከ90 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ስለ ለውጡ መረጃ መስጠት።

T. የልጁን ወይም የወጣቱን የህክምና መዝገቦች በሚስጥር እንዲጠበቁ እና ከወላጅ፣ ህጋዊ አሳዳጊ ወይም ከሞግዚት ነፃ ከወጣው አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ በጽሁፍ የሰጠ ፈቃድ ሲኖር ብቻ እንዲለቀቅ ማድረግ።

U. የሱን ወይም የሷን የሕክምና ሪከርዶችን መጠየቅ እና ቅጂውን መቀበል መቻል፣ እና በ 45C.F.R ክፍል 164.524 እና 164.526 ላይ በተገለጸው መሠረት እንዲሻሻል ወይም እንዲታረም መጠየቅ።

V. የልጅዎ የእንክብካቤ መረጃ በህጋዊ ጥያቄ መሠረት ከተለቀቀ በ 10 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ እንዲያዉቁት መደረግ።

W. ልጁ ወይም ወጣቱ በህክምና፣ ቃለ መጠይቆች እና ማንኛውም የእንክብካቤ እቅድ ስብሰባዎች ላይ ግላዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ተገቢ የሆነ የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ።

X. ለልጁ ወይም ወጣቱ በቀን 24 ሰዓታት፣ በዓመቱ እያንዳንዱን ቀን የHSSN የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማድረግ።

Y. ተመዝጋቢዎች/ተንከባካቢዎች በማንኛውም ምክንያት ያለመገደድ ወይም ትዝብት ውስጥ ያለመውደቅ መብት አላቸው።

Z. እንግሊዝኛ የማይናገሩ ተመዝጋቢዎች የትርጉም አገልግሎት ያገኛሉ።

AA. ተመዝጋቢዎች በሌሎች ቋንቋዎች እና ቅርጸቶች ሰነዶች ይተረጎምላቸዋል።

BB. LEP ያለው ተመዝጋቢ የቃል የትርጉም አገልግሎቶች በጊዜው ካልተሰጡ አቤቱታ የማቅረብ መብት አላቸው።

CC: ለዲስፕሊን ወይም ለበቀል ዓላማ ከሚደረጉ ክልከላዎች ነጻ የመሆን መብት።

DD. የHSCSN የፋይናንስ ሁኔታን ማወቅ። ተመዝጋቢዎች የHSCSN እዳዎች ወይም ሀብቶች ላይ ሀላፊነት አይኖርባቸውም፤ እና ሽፋን ላላቸው አገልግሎቶች የመክፈል ሀላፊነት አይኖርባቸውም።

EE. ስለ HSCSN የሀኪም ትእዛዝ የሚያስፈልጋቸው የመድሃኒት ፕሮግራም ፖሊሲ፣ መድሃኒቱ ላይ ቅሬታ ወይም የይግባኝ ሂደት እየተካሄደ ባለበት ወቅት ተመዝጋቢው መድሃኒቱን የማግኘት መብት እንዳለው የማወቅ መብት።

FF. የPHSCSN የሃኪም የጥቅማጥቅም እቅዶች (PIPs) መግለጫ።

GG በ42 C.F.R. sec. 438.10(i)(3)(iv) ላይ በተገኙት መሥፈርቶችን መሠረት በማድረግ ማንኛውም የተመዝጋቢ እርካታ የዳሰሳ ጥናት መግለጫዎች።

| 18 አመት ወይም ከዚያ በታች | • MCV4 |
| በየ 6 ወር | • የጥርስ ህክምና ጉብኝቶች |
| በየአመቱ | • ጉንፋን |

## የእድገት ጉዞ መንገዶች

ይህ ሰንጠረዥ ልጅዎ የእድገት መዘግየት እንዳለው/ላት ለማወቅ ሊረዳዎት ይችላል። እንደ መመሪያ ይጠቀሙት። ልጅዎ በተመሳሳይ እድሜ ላይ ካሉ ሕፃናት ትንሽ ቀደም ብሎ ወይም ዘግይቶ እነዚህ የእድገት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል። ማንኛውም ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ካሉዎት ከልጅዎ ሀኪም ጋር ተነጋገሩ።

| | |
|---|---|
| **በ 7 ወራት መጨረሻ፣ብዙ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥**<br>• ስማቸው ሲጠራ ጭንቅላታቸውን ማዞር።<br>• ለሌላ ሰው አጸፋዊ ፈገግታ መስጠት።<br>• ድምፅን በድምፅ መመለስ።<br>• እንደ ፒክ-ኤ-ቡ (አየሁህ/ሽ) ያሉ የማህበራዊ ጨዋታ መደሰት። | **በ 2 ዓመታት መጨረሻ (24 ወራት)፣ ብዙ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥**<br>• ከ 2- እስከ 4-ቃላት ሐረጎች መጠቀም።<br>• ቀላል መመሪያዎችን መከተል።<br>• ሌሎች ሕፃናት ላይ ፍላጎት ማሳየት።<br>• ሲጠሩ ዕቃ ወይም ስዕልን ላይ ጣት ማቅሰር። |
| **በ 1 ዓመት መጨረሻ (12 ወራት)፣ ብዙ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥**<br>• ቀላል ምልክቶችን መጠቀም፣ የ"ቻው-ቻው" እጅ ማንሳት።<br>• እንደ "ማ" እና "ዳ" ያሉ ድምጾችን ማሰማት።<br>• በጨዋታቸው ውስጥ ድርጊቶችን ማስመሰል (እርስዎ እጅ ሲያጨበጭቡ እነሱም ማጨብጨብ)።<br>• "ተው" ሲባሉ መልስ መስጠት። | **በ 3 ዓመታት መጨረሻ (36 ወራት)፣ ብዙ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥**<br>• አብረው ለሚጫወቱት ፍቅር ማሳየት።<br>• ከ 4- እስከ 5-ቃላት ዓረፍተ-ነገሮችን መጠቀም።<br>• አዋቂዎችን እና አብረው የሚጫወቱትን ማስመሰል (ሌሎች ልጆች ሲሮጡ መሮጥ)።<br>• በአሻንጉሊቶች፣ እንስሳት፣ እና ሰዎች እቃ እቃ መጫወት (ቴዲ ቤርን "መመገብ")። |
| **በ 1½ ዓመታት መጨረሻ (18 ወራት)፣ ብዙ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥**<br>• ቀላል የማስመሰል ጨዋታን መጫወት (የአሻንጉሊት ስልክ ላይ "ማውራት")።<br>• ደስ የሚሉ ዕቃዎችን መጥቆም።<br>• ወደ ዕቃ ጣት ቀስረው እነሱ እንዲያዩ ሲነግሯቸው ወደ ዕቃው ማየት።<br>• ግፊት ሳይደረግባቸው በርካታ ነጠላ ቃላትን መጠቀም። | **በ 4 ዓመታት መጨረሻ (48 ወራት)፣ ብዙ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥**<br>• ከ 4- እስከ 6-ቃላት ዓረፍተ-ነገሮችን መጠቀም።<br>• ባለ 3-ደረጃ ትዕዛዞችን መተግበር ("ልብስ መልበስ፣ ጸጉርህን አበጥር እና ፊትህን ታጠብ")።<br>• ከሌሎች ሕፃናት ጋር መተባበር። |

# የጤና ጥቅሞችዎ

## በ HSCSN የሚሸፈኑ የጤና አገልግሎቶች

ከዚህ በታች ያለው ዝርዝር የሁሉንም የ HSCSN ተመዝጋቢዎች የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች እና ጥቅማጥቅሞችን ያሳያል። አንዳንድ ጥቅሞችን ለማግኘት የተወሰነ የእድሜ ክልል ውስጥ መሆን ወይም አገልግሎቱ በተወሰነ መልኩ ለእርስዎ አስፈላጊ የሆነ መሆን አለበት። እርስዎ ኔትዎርክ ውስጥ ወዳለ አቅራቢ ወይም ሆስፒታል ከሄዱ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ላሉ ማንኛውም የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች HSCSN አያስከፍልዎትም።

HSCSN የተወሰነ የጤና እንክብካቤን ይሸፍን እንደሆነ እና አገልግሎቶችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ጥያቄ ካሉት፣ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

| ጥቅሞች | የሚያገኙት ምንድን ነው | ይህንን ጥቅም ማን ሊያገኝ ይችላል |
|---|---|---|
| **የአዋቂዎች የደህንነት አገልግሎቶች** | • ክትባቶች<br>• በግብረስጋ ግንኙነት ለሚከሰቱ በሽታዎች መደበኛ ምርመራ<br>• HIV/AIDS ምርመራና የምክር አገልግሎት<br>• የጡት ካንሰር ምርመራ<br>• የማህጸን ካንሰር ምርመራ (ለሴቶች ብቻ)<br>• የኦስቴፖሮሲስ ምርመራ (ላረጡ ሴቶች)<br>• የኤችፒቪ (HPV) ምርመራ<br>• የፕሮስቴት ካንሰር ምርመራ (ለወንዶች ብቻ)<br>• የሆድ ኦሮቲክ አንዬሪዝም ምርመራ<br>• ከልክ በላይ ውፍረት (Obesity) ምርመራ<br>• የስኳር ህመም ምርመራ<br>• የከፍተኛ የደም ግፊትና የኮሌስትሮል ምርመራ (የሊፒድ ችግሮች)<br>• የጭንቀት ምርመራ<br>• የኮሎሬክታል ካንሰር ምርመራ (50 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ተመዝጋቢዎች)<br>• ማጨስ ስለማቆም የምክር አገልግሎት<br>• የአመጋገብና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ምክር<br>• የአእምሮ ጤና የምክር አገልግሎት<br>• መጠጥ እና ሌሎች ዕጾች መውሰድ ምርመራ | እድሜያቸው ከ 21 ዓመት በላይ ለሆኑ ተመዝጋቢዎች እንደአስፈላጊነቱ |

| ጥቅሞች | የሚያገኙት ምንድን ነው | ይህንን ጥቅም ማን ሊያገኝ ይችላል |
|---|---|---|
| **የአልኮልና የአደንዛዥ እጽ ሱስ ህክምና** | • ተኝቶ የሚታከም ታካሚ ከሱስ ነጻ ማድረግ<br>• ሌሎች የአልኮል/የአደንዛዥ እጽ ሱስ ህክምና አገልግሎቶች በሱስ መከላከልና ማገገም አስተዳደር (DBH)።<br>• ከ DBH እንክብካቤ ለማገኘት እገዛ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| | • የተመላላሽ እና የውስጥ ታካሚ የእጽ ሱስ ሕክምና<br>• ሌሎች የአልኮል/የአደንዛዥ እጽ ሱስ ህክምና አገልግሎቶች በሱስ መከላከልና ማገገም አስተዳደር (DBH)።<br>• ከ DBH እንክብካቤ ለማገኘት እገዛ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የህጻናት የደህንነት አገልግሎቶች** | ምርመራዎችንና ግምገማዎችን ጨምሮ፣ የታመሙ ህጻናትን ለመንከባከብና ጤናማ ህጻናትን በጤና ለማቆየት የሚከተሉትን የመሳሰሉ አስፈላጊ ነገሮች፣<br>• የጤናና የእድገት ታሪክ ምርመራ<br>• የአካላዊና የአእምሮ ጤና እድገትና ምርመራ<br>• አጠቃላይ የጤና ምርመራ<br>• ክትባቶች<br>• የደም መጠንን ጨምሮ የላብራቶሪ ምርመራዎች<br>• የጤና ትምህርት<br>• የጥርስ ህክምና ምርመራ አገልግሎት<br>• የአይን ህክምና ምርመራ አገልግሎት<br>• የመስማት ህክምና ምርመራ አገልግሎት<br>• የአልኮልና የአደንዛዥ እጽ የምክር አገልግሎትና ምርመራ<br>• የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች<br>ለልጁ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጡ ማናቸውንም የጤና አገልግሎቶች አይጨምርም። | እድሜያቸው ከ21 በታች የሆኑ ተመዝጋቢዎች |

| ጥቅሞች | የሚያገኙት ምንድን ነው | ይህንን ጥቅም ማን ሊያገኝ ይችላል |
|---|---|---|
| **የጥርስ ህክምና ጥቅሞች** | • አጠቃላይ የጥርስ ህክምና (መደበኛና የድንገተኛ ህክምናን ጨምሮ) እና ኦርቶዶንቲክ ህክምና (ጥርስ ላይ ያሉ ችግሮችን ለማስተካከል)<br>• እድሜያቸው ሶስት (3) እስከ ሃያ አምስት (25) ለሆኑ ልጆች በየስድስት (6) ወሩ የጥርስ ሀኪም ክትትል ይሸፈናል።<br>• የልጅዎ PCP እድሜያቸው እስከ 3 ለሆኑ ህጻናት የጥርስ ምርመራ ማድረግ ይችላል<br>• መደበኛ የኦርቶዶንቲክ ህክምናን አይጨምርም<br>• የፍሎራይድ ቫርኒሽ ህክምና እስከ አራት (4) ጊዜ ድረስ በዓመት እድሜያቸው ከሰስት (3) በታች ለሆኑ ተመዝጋቢዎች። | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| | • አጠቃላይ የጥርስ ምርመራዎች እና መደበኛ ማጽዳት በየስድስት (6) ወራት<br>• የቀዶ ጥገና አገልግሎቶችና የጥርስ መነቀሎች<br>• የድንገተኛ ጊዜ የጥርስ ህክምና<br>• መሙላት<br>• ኤክስሬይ (ሙሉ ዙር ለአንድ (1) ጊዜ ብ ቻ በየሶስት (3) ዓመታት)<br>• ሙሉ የአፍ ውስጥ የማደስ ህክምና (mouth debridement)<br>• ፕሮፊላክሲስ በየስድስት (6) ወራት አንድ (1) ጊዜ ብቻ<br>• ባይትዊንግ ሲሪስ (Bitewing series)<br>• ፓሊዬቲቭ (Palliative) ህክምና<br>• ሲላንት (Sealant) ማድረግ<br>• እድሜያቸው ሃያ (20) ዓመት እና ከዚያ በታች ለሆኑ ተመዝጋቢዎች በከፊል እና በሙሉ የሚወገድ<br>• የሩት ካናል ህክምና<br>• ፔሪዮዶንታል (Periodontal) ማስተካከልና ስር ማስተካከል<br>• ጥርስ ላይ የሚገጠሙ መከላከያዎች (Dental crowns)<br>• የተበላሹ ጥርሶች ነቀላ<br>• የሚነቀል ፕሮስተሲስ (prosthesis) የመጀመሪያ ተከላ (አንድ ወይም ከዚያ በላይ የወለቀ ጥርስን ለመተካት የሚገጠም ማንኛውም የጥርስ መሳሪያ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ማውለቅ እና መልሶ መግጠም እንዲቻል ሆኖ የተሰሩ ተያያዥ እቃዎችን ጨምሮ)፣ በየአምስት (5) ዓመት አንድ ጊዜ። አንዳንድ ገደቦች ሊተገበሩ ይችላሉ።<br>• የሚነቀል ከፊል ፕሮስተሲስ፤ ቅድመ ፈቃድ ከሌለ በስተቀር<br>• በሆስፒታል ተኝቶ የሚደረግ ማንኛውም የጥርስ ህክምና አገልግሎት ቅድሚያ ፈቃድ ያስፈልጋል (ቅድመ ፈቃድ)፤ የተወሰኑ ገደቦች ሊኖሩ ይችላሉ | እንደ አግባብነቱ፣ እድሜያቸው ሃያ አምስት (25) እና ከዚያ በታች |

| ጥቅሞች | የሚያገኙት ምንድን ነው | ይህንን ጥቅም ማን ሊያገኝ ይችላል |
|---|---|---|
| **የዲያሊሲስ አገልግሎት** | • በሳምንት እስከ 3 ጊዜ ድረስ ህክምና (በቀን አንድ ጊዜ ብቻ) | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **ረጅም ጊዜ የሚቆዩ የህክምና መሳሪያዎች (DME) እና አላቂ የህክምና እቃዎች (DMS)** | • ረጅም ጊዜ የሚቆይ የህክምና መሳሪያ Durable medical equipment (DME)<br>• አላቂ የህክምና ግብዓቶች (DMS) | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የድንገተኛ አገልግሎቶች** | • አቅራቢው በኛ የHSCSN ኔትዎርክ ውስጥ ይሁንም አይሁን፤ ድንገተኛ የሕክምና ሁኔታ ካለብዎ የጤንነት ሁኔታ ምርመራ፣ የድህረ ማረጋጋት አገልግሎቶች፣ እና የማረጋጋት አገልግሎቶች።<br>• ለድንገተኛ ሁኔታዎች ህክምና | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የቤተሰብ እቅድ** | • የእርግዝና ምርመራ፣ የምክር አገልግሎት ለሴቶች<br>• መደበኛ እና ድንገተኛ የወሊድ ቁጥጥር አገልግሎት<br>• እድሜያቸው ከ21 ዓመት በላይ ለሆኑ አባላት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ማምከን (ህክምናው ከመደረጉ ከ30 ቀናት በፊት በአባሉ የጸደቀ እና የተፈረመ የማምከን አገልግሎት ቅጽ ይጠይቃል)<br>• ምርመራ፣ የምክር አገልግሎትና ክትባቶች (ሂዩማን ፓፒሎማ ቫይረስ (Human Papilloma Virus — HPV) ጨምሮ)<br>• በግብረስጋ ለሚተላለፉ ሁሉም በሽታዎች ምርመራ እና የመከላከል ሕክምና<br>እድሜያቸው ከ21 በታች ለሆኑ ተመዝጋቢዎች የማምከን ህክምና መስጠትን አያካትትም | እንደ አግባብነቱ ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የመስማት ጥቅማጥቅሞች** | • የመስማት ህክምና ምርምራዎች እና አገልግሎቶች፣ ከመስማት ማገዣ መሳሪያዎች እና ባትሪዎቻቸውን ጨምሮ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የቤት ውስጥ የጤና አገልግሎቶች** | የሚከተሉትን ጨምሮ የቤት ውስጥ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች፣<br>• የነርስ አግልገሎትና የቤት ውስጥ ተንከባካቢ ህክምና<br>• የቤት ውስጥ ጤና እርዳታ አገልግሎቶች በቤት የጤና ኤጀንሲ የሚሰጥ<br>• አካላዊ ቴራፒ፣ አእምሮአዊ ቴራፒ፣ የንግግር ፓቶሎጂና የድምጽ አገልግሎት | ሁሉም ተመዝጋቢዎች እንደ አግባብነቱ |
| **የደከሙ ሰዎች እንክብካቤ (Hospice Care)** | • የሕይወት መጨረሻ ላይ ላሉ ሰዎች የሚሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች እንደ አግባብነቱ |

| ጥቅሞች | የሚያገኙት ምንድን ነው | ይህንን ጥቅም ማን ሊያገኝ ይችላል |
|---|---|---|
| **የሆስፒታል አገልግሎቶች** | • ተመላላሽ ታካሚዎች (የመከላከል፣ ምርመራ፣ ቴሮፓውቲክ፣ የመልሶ ማገገም፣ ወይም የፓሊያቲቭ አገልግሎቶች)<br>• የተኝቶ ታካሚ አገልግሎቶች (ሆስፒታል ውስጥ የሚቆዩ) | ከ PCP ሪፈራል ያላቸው ወይም የአስቸኳይ ሁኔታ ያለው ማንኛውም ተመዝጋቢዎች |
| **ላብራቶሪ እና የኤክስሬይ አገልግሎቶች** | • የላብራቶሪ ምርመራዎችና ራጆች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች** | • በአዕምሮ ጤና አገልግሎት አቅራቢዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች፣ የሚከተሉትን ያካትታሉ፣<br>  ○ የምርመራና የግምገማ አገልግሎቶች<br>  ○ የሀኪም እና የመካከለኛ ደረጃ ጉብኝቶች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ:<br>  ○ የግል የምክር አገልግሎት<br>  ○ የቡድን የምክር አገልግሎት<br>  ○ የቤተሰብ የምክር አገልግሎት<br>  ○ FQHC አገልግሎቶች<br>• የመድሃኒት/ሶማቲክ ህክምና<br>• የቀውስ አገልግሎቶች<br>• በሆስፒታል ተኝቶ መታከም እና የድንገተኛ ክፍል አገልግሎቶች<br>• ጥልቅ የቀን ህክምና<br>• የእንክብካቤ አስተዳደር አገልግሎቶች<br>• እርግዝናን ሊያወሳስብ የሚችል ማንኛውም የአዕምሮ ሁኔታ ሕክምና<br>• እድሜያቸው ከ22 በታች ለሆኑ ተመዝጋቢዎች ለሰላሳ (30) ተከታታይ ቀናት የታካሚ የሳይኪያትሪክ ሬዚዴንሺያል የህክምና ተቋም አገልግሎቶች (PTRF)<br>• በ IEP ወይም IFSP ውስጥ ለተካተቱ ህጻናት በበዓል ቀናት፣ ትምህርት ዝግ በሚሆንበት ጊዜ፣ ወይም ታመው ከትምህርት ቤት በሚቀሩበት ጊዜ የሚሰጡ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች<br>• ከ DBH የሚከተሉትን አገልግሎቶች የሚያገኙ ተመዝጋቢዎች የእንክብካቤ ቅንጅት፣<br>  ○ ማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ የመፍትሄ እርምጃዎች<br>  ○ ባለብዙ ስርዓት ህክምና (Multi-systemic therapy (MST))<br>  ○ አሰርቲቭ ኮሚዩኒቲ ትሪትመንት (Assertive community treatment (ACT))<br>  ○ የማህበረሰብ ድጋፍ<br>• የአእምሮ ጤና እና የእጽ ሱስ አገልግሎቶች በአእምሮ በሽታ ተቋም ዉስጥ | እንደ አግባብነቱ፣ ሁሉም ተመዝጋቢዎች |

| ጥቅሞች | የሚያገኙት ምንድን ነው | ይህንን ጥቅም ማን ሊያገኝ ይችላል |
|---|---|---|
| **የግል እንክብካቤ አገልግሎቶች** | • እንደዚህ አይነት አገልግሎቶችን የመስጠት ብቃት ባለው የተመዝጋቢው ቤተሰብ አባል ባልሆነ ግለሰብ የተሰጡ አገልግሎቶች፣ አብዛኛውን ጊዜ ቤት ውስጥ፣ እና በተመዝጋቢው የእንክብካቤ እቅድ ላይ እንደተካተተው በሀኪሙ ፈቃድ።<br>• ይህንን አገልግሎት ለማግኘት አስቀድመው ፈቃድ መገኘት አለብዎ። | ተገቢ የሆነ የህክምና ምክንያት ያላቸው ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች (በማዘዣ የሚሸጡ መድሃኒቶች)** | • በ HSCSN የመድሃኒት ቅመማ ላይ የተካተቱ በሀኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶች የመድሃኒቱን ቅመማ በ www.hscsnhealthplan.org or ወይም ወደ ደምበኛ አገልግሎቶች በመደወል ሊያገኙ ይችላሉ።<br>• በኔትወርክ ውስጥ ካሉ መድሃኒት ቤቶች የሚሰጡ መድሃኒቶችን ብቻ ያካትታል<br>• የሚከተሉትን በሐኪም ትዕዛዝ የማይታዘዙ (ከመድሐኒት መደብር የሚገዙ) መድሐኒቶች ያካትታሉ። ያለ ማዘዣ የሚሸጡ መድሃኒቶችን ለማግኘት ከሃኪምዎ የመድሃኒት ማዘዣን ማግኘት አለብዎ። ሙሉ ዝርዝሩ በ www.hscsnhealthplan.org ወይም የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር በመደወል ይገኛል። | በሁለት ምክንያት ብቁ ከሆኑ ውጪ ሁሉም ተመዝጋቢዎች (Medicaid/ Medicare) ተመዝጋቢዎች በሀኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶቻቸው በ Medicare Part D የሚሸፈን |
| **የእግር ህክምና (Podiatry)** | • ከእግር ጋር ለተያያዙ ችግሮች ልዩ ህክምና<br>• በህክምና አስፈላጊ ሲሆን መደበኛ የእግር ህክምና | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና አገልግሎቶች** | • የመከላከል፣ የከፋ፣ እና ስር የሰደዱ የጤና ሕክምና አገልግሎቶች በእርስዎ PCP የሚቀርቡ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **ፕሮስቴቲክ መሳሪያዎች (Prosthetic Devices)** | • ፈቃድ ባለው አቅራቢ የታዘዙ የመተኪያ፣ የማስተካከያ ወይም የሚደግፉ መሳሪያዎች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የማገገም (Rehabilitation) አገልግሎት** | • አካላዊ፣ የንግግር እና የስራ ቦታ ህክምናን ያካትታል | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |

| ጥቅሞች | የሚያገኙት ምንድን ነው | ይህንን ጥቅም ማን ሊያገኝ ይችላል |
|---|---|---|
| **የስፔሺያሊስት አገልግሎቶች** | • ልዩ ስልጠና ባገኙ ዶክተሮች ወይም በከፍተኛ ደረጃ ነርሶች የሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች<br>• ሪፈራሎች አብዛኛውን ጊዜ ያስፈልጋሉ።<br>• ከቀዶ ጥገና ወይም ከህመም ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ሁኔታዎችን ለማስተካከል፣ በድንገተኛ አደጋ ጉዳት ወይም ሲወለዱ የነበሩ ችግርን፣ ወይም አካልዎ በመደበኛ ሁኔታ እንዳይሰራ እክል የሚፈጥርን ችግር ለማስተካከል ከሚደረጉ ቀዶ ጥገናዎች በስተቀር የውበት አገልግሎቶችንና ቀዶ ህክምናን (Cosmetic surgery) አያጠቃልልም | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የትራንስፖርት አገልግሎቶች** | • በ DHCF የሚሸፈኑ አገልግሎቶችን ጨምሮ ወደ እና ከህክምና ቀጠሮዎች ለሚያስፈልግ ትራንስፖርት | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የአይን ህክምና** | • በየአመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ እና እንዳስፈላጊነቱ የሚሰጥ የዓይን ምርመራዎች። | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| | • በየዓመቱ አንድ (1) የዓይን መነጽር፤ አባሉ መነጽር ካልጠፋበት/ካልጠፋበት ወይም ትዕዛዙ ከ 0.5 ዲዮፕተር (diopter) በላይ ካልጨመረ በስተቀር | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |



## የማንከፍልባቸው አገልግሎቶች

- የውበት ቀዶ ህክምና (Cosmetic surgery)
- የሙከራ ወይም የምርምር አገልግሎቶች፣ ቀዶ ጥገናዎች፣ ህክምናዎችና መድሃኒቶች
- የክሊኒካል ሙከራ ፕሮቶኮል አካል የሆኑ አገልግሎቶች
- ውርጃ፣ ወይም በፈቃደኝነት ጽንስ ማስወገድ፤ በፌደራል ህግ መሠረት የማይጠየቅ
- አገልግሎቱ የውርጃ ነው፤ ከሚከተለው በስተቀር፣
  - ጽንሱ እስከ ሙሉ የእርግዝና ወቅት ቢቆይ የእናትየው ህይወት አደጋ ላይ የሚሆን ከሆነ።
  - እርግዝናው በአስገድዶ መድፈር ወይም በዘመዳሞች መካከል በተደረገ የግብረ ስጋ ግንኙነት የተፈጠረ ከሆነ።
- የመሃንነት ህክምና
- እድሜያቸው ከ21 አመት በታች ለሆኑ ሰዎች የማምከን ህክምና
- በህክምና አስገዳጅ ያልሆኑ አገልግሎቶች።
- አንዳንድ የምክር ወይም የሪፈራል አገልግሎቶች በሃይማኖት ወይም የሞራል እምነቶች ምክንያቶች በHSCSN አይሸፈኑም። ለተጨማሪ መረጃ DHCFን በ (202) 442-5988 ያግኙ።
- አገልግሎቱ የተሸፈኑ ጥቅማጥቅሞች ዝርዝር ውስጥ አልተገለጸም እና የቅድመ ፈቃድ የለውም።
- ቀዶ ጥገናው እና/ወይም ምርቶቹ ለቁንጅና ምክንያቶች ናቸው (ከታች ይመልከቱ)።
- አገልግሎቱ በመጠን፣ ቆይታ፣ እና ስፋት በ D.C. የጤና እንክብካቤ የፋይናንስ በግልጽ ከተቀመጠው ገደብ በላይ ነው።
- አገልግሎቱ ለ Medicare እና D.C.Medicaid ለሁለቱም ብቁ ለሆነ ተመዝጋቢ የሚሰጥ የሀኪም ትዕዛዝ ያለው መድሃኒት ነው። እነዚህ መድሃኒቶች ለብቻ የሚታዩ ናቸው፥
  - ቤንዞዲያዜፒነስ (Benzodiazepines)
  - ባርቢቱራተስ (Barbiturates)
  - የተሸፈኑ ያለ-ትዕዛዝ-የሚሰጡ መድሃኒቶች።

**አገልግሎቱ፥**

  - የምርመራ
  - የሙከራ
  - የክሊኒካል ሙከራ አካል።
- አገልግሎቶቹ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ሰራተኞች፣ ወይም ከትምህርት ቤቱ ጋር ኮንትራት ያላቸው፣ ወይም ተመዝጋቢው የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ከሆነ።

## የእንክብካቤ ሽግግር

HSCSN ለእርስዎ አዲስ ከሆነ፣ ለመጀመሪያዎቹ 90 ቀናት ውስጥ የተያዘውን የሀኪም ቀጠሮዎች እና የመድሃኒት ማዘዣዎችን እንደያዙ ማቆየት ይችላሉ። ባሁኑ ጊዜ አቅራቢዎ በ HSCSN ኔትዎርክ ዉስጥ ከሌለ፣ በHSCSN ኔትዎርክ ውስጥ ያለ አዲስ አቅራቢ እንዲመርጡ ሊጠየቁ ይችላሉ።

ሀኪምዎ HSCSN ኔትዎርክ ከለቀቁ፣ ሌላ አቅራቢ ለመምረጥ ጊዜ እንዲኖሮት በ15 የካላንደር ቀናት ውስጥ እናሳውቅዎታለን። HSCSN አቅራቢዎ ጋር ያለውን ውል ካቋረጠ፣ መቋረጡ ሥራ ላይ ከሚውልበት ከ30 የካላንደር ቀናት በፊት እናሳውቅዎታለን።

ከ24ኛ ዓመትዎ ጀምሮ፣ የእርስዎ እንክብካቤ አስተዳዳሪ ከእድሜ-ውጭ የሚያደርጉትን የሽግግር እቅድ ለማዘጋጀት ከእርስዎ ጋር በቅርበት ይሰራል። የእንክብካቤ አስተዳዳሪ የሚከተሉትን ያደርጋል፦

- የሁሉም አገልግሎቶች እና አቅራቢዎችዎን ዝርዝር እንዳገኙ ያረጋግጣል። ይህ የሚጨምረው፥
  - ሀኪሞች
  - መድሃኒቶች እና ግብዓቶች
  - የቤት ውስጥ ሕክምና አገልግሎቶች
  - የህክምና መሳሪያ
- ወደ FFS Medicaid አቅራቢዎች እንደቀየሩ ያረጋግጣል።
- የ FFS Medicaid መታወቂያ ካርድን ለመጠየቅ ከእርስዎ ጋር ይሰራል።
- የእርስዎ FFS Medicaid ብቁነት ከ D.C. የኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር ጋር ወቅታዊ መሆኑን ማረጋገጥ።
- የእርስዎ FFS Medicaid ብቁነትን ዳግም እንዲያረጋግጡ ያግዝዎታል።
- ብቁ ሊሆኑበት ስለሚችሉ የ D.C. አካል ጉዳተኝነት አገልግሎቶች ዲፓርትመንት ፕሮግራሞች ከእርስዎ ጋር ይነጋገራል እና በፕሮግራም ማመልከቻዎች ያግዝዎታል።
- የማህበረሰብ ግብዓቶች ዝርዝር ያሎት መሆኑን ያረጋግጣል።
- በሽግግርዎ ጊዜ ሊታዩ የሚችሉ ችግሮችን እንዴት እንደሚያስተካክሉ ያውያያል።

ከ HSCSN ሲወጡ የእንክብካቤ ቅንጅት ድጋፍን ለአዋቂዎች የሚሰጡ የእንክብካቤ አስተዳደር ኤጀንሲ ውስጥ መመዝገብ ይችሉ ይሆናል። የእርስዎ HSCSN እንክብካቤ አስተዳዳሪ እንዴት እንደሚመዘገቡ ከእርስዎ ጋር ይወያያል። ብቁ ከሆኑ፣ይህ ለውጥ ብዙውን ጊዜ ከ HSCSN ከወጡ በኋላ 30-60 ቀናት ውስጥ ይከናወናል።

ከ HSCSN በእድሜ ምክንያት ስለ መውጣት ጥያቄዎች ካሎት፣ እባክዎ በ (202) 467-2737 ይደውሉ እና የጉዳይ አስተዳዳሪዎን ለማነጋገር ይጠይቁ።

HSCSN ኢንሹራንስ እድሜያቸው ከ 26 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ እና አዋቂዎች ነው። እርስዎ 26 ዓመት ሲሞላዎ ከHSCSN አባልነት ይወጣሉ።

# ማወቅ የሚገባዎ ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች

## አድራሻ ከቀየርኩ ምን ማድረግ አለብኝ

- የኮሎምቢያ ዲስትሪክት(ዲሲ) የኢኮኖሚያዊ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል ጋር ይደውሉ በ 202-727-5355።
- ለ HSCSN ደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

## ልጅ ከወለድኩ ምን ማድረግ አለብኝ

- ለዲሲ የኢኮኖሚያዊ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል በ202-727-5355 ይደውሉ
- ለ HSCSN ደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

## ልጅ በጉዲፈቻ ከወሰድኩ ምን ማድረግ አለብኝ

- ለዲሲ የኢኮኖሚያዊ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል በ202-727-5355 ይደውሉ

## ከቤተሰቤ ውስጥ አንድ ሰው ከሞተ ምን መድረግ አለብኝ

- ለዲሲ የኢኮኖሚያዊ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል በ202-727-5355 ይደውሉ
- ለ HSCSN ደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

## የእኔን MCO እንዴት መቀየር እንደምችል

- በዓመት አንድ ጊዜ የእርስዎን MCO መቀየር ይችላሉ፣ ወይም በቂ ምክንያት ካሉት በማንኛውም ጊዜ።
  - ከአገልግሎት አካባቢ ወደ ሌላ ቦታ ከተዘወሩ፣
  - HSCSN በሞራል ወይም ሃይማኖታዊ ምክንያቶች፣ የሚፈልጉትን አገልግሎት(ቶች) አይሸፍንም፣
  - ተያያዥ የሆኑ አገልግሎቶች በተመሳሳይ ጊዜ እንዲከናወኑ ከፈለጉ እና ተያያዥ የሆኑ ሁሉም አገልግሎቶች የማይገኙ ከሆነ እና አቅራቢዎ አገልግሎቶቹን ለየብቻ ማግኘት አደጋ እንዳለው ከወሰኑ።
  - በዘር፣ ጾታ፣ ብሄር፣ የብሄራዊ አመጣት፣ ሃይማኖት፣ አካል ጉዳተኝነት፣ እርግዝና፣ እድሜ፣ የዘረመል መረጃ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የወሲባዊ ምርጫ፣ የጾታ መለያ፣ የግል መግለጫ፣ የቤተሰብ ሀላፊነቶች፣ የፖሊቲካ አመለካከት፣ እና/ወይም የገቢ ምንጭ ወይም የመኖሪያ ቦታ፣ MCO አድልዎ እንደፈጸመብዎ ካመኑ፤ ወይም፣
  - አነስተኛ ጥራት ያለው እንክብካቤ እንዳገኙ፣ ሽፋን ያላቸውን አገልግሎቶች ማግኘት እንዳልቻሉ፣ ወይም የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችዎን ለማስተናገድ ልምድ ያላቸው አቅራቢዎች ማግኘት እንዳልቻሉ ካመኑ።
- የእርስዎን MCO በዓመት አንድ ጊዜ መቀየር ይችላሉ፣ መቀየር የሚችሉትም ወደ HSCSN የገቡበት ወር እና ቀን አመታዊ በዓል ከመድረሱ በፊት ባሉት 90 የካላንደር ቀናት ውስጥ ነው።
- የመጀመሪያ ምዝገባ ቀንዎ በኋላ በ90 የካላንደር ቀናት ውስጥ ወይም ከዲስትሪክቱ የምዝገባ ማስታወቂያ ከደረሰዎ በኋላ በ90 ካሌንደር ቀናት ውስጥ፣ የትኛውም በኋላ የመጣ።
- ከዚያ በኋላ ቢያንስ በየ 12 ወራት።

- ጊዜያዊ የብቁነት ማጣት ዓመታዊ ያለመመዝገብ እድል እንዲያጡ ካደረገ።
- ዲስትሪክቱ በHSCSN ላይ ማዕቀቦች ከጣለ፣ ምዝገባን ማገድ።
- D.C. Healthy Families ከዓመት በዓል ማክበሪያ ቀንዎ ሁለት ወራት አስቀድሞ ደብዳቤ ይልክልዎታል። ደብዳቤው እንዴት MCO መለወጥ እንደሚችሉ ይነግርዎታል።
- የሚፈልጉትን እንክብካቤ ማግኘት መቀጠል እንዲችሉ፣የጤና እንክብካቤ መረጃዎ ወደ የመረጡት አዲሱ MCO ይተላለፋል።

## የሚከተሉትን ካደረጉ፣ ከእንግዲህ የጤና እንክብካቤን ከ HSCSN እንዲያገኙ አይፈቀድልዎትም፥

- ለ Medicaid ብቁ የሚያደርጉዎትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ካቆሙ።
- የማህበራዊ ዋስትና ገቢ (SSI) ብቁነት ካቆሙ።
- የረባሽ ወይም በዳይ ባህሪይ አካሄድ ካሳዩ፣ ወይም በማጭበርበር ወይም በማታለል አገልግሎቶች ከወሰዱ።

## የ D.C. መንግስት እርስዎን ከ HSCSN ሊሰርዝዎ ይችላል፣ የሚከተሉትን ካደረጉ፥

- ሌላ ሰው የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን እንዲጠቀምበት ካደረጉ፣
- ዲስትሪክቱ የMedicaid የማጭበርበር ተግባር እንደፈጸሙ ካወቀ፣ ወይም
- የተመዝጋቢ ሃላፊነቶችዎን ካልተወጡ።

## ሽፋን ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቢል ከቀረበልኝ ምን ማድረግ አለብኝ

ከላይ በተገለፀው ዝርዝር ውስጥ ለተሸፈነው አገልግሎት ደረሰኝ ከደረስዎ፣ ለደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

## ሽፋን ለማይሰጣቸው አገልግሎቶች መክፈል

- እኛ የማንከፍልበትን አገልግሎት እንደሚፈልጉ ከወሰኑና ከ HSCSN የተሰጠ የጽሁፍ ፈቃድ ከሌለዎት፣ ለአገልግሎቱ እራስዎ መክፈል ይኖርብዎታል።
- እኛ የማንከፍልበትን አገልግሎት እንደሚፈልጉ ከወሰኑ ለአገልግሎቱ እራስዎ እንደሚከፍሉ የሚያሳይ መግለጫ ላይ መፈረም አለብዎ።
- ሁልጊዜም የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን ማሳየት እንዳለብዎና አገልግሎቱን ከማግኘትዎ በፊት ለሀኪሞች የ HSCSN ተመዝጋቢ መሆንዎን መንገር አይርሱ።
- እርስዎ ለአገልግሎቶች ከከፈሉ እና ተመላሽ የማግኘት መብት እንዳሎት ካመኑ፣ ወደ መድሃኒት ቤቱ፣ ክሊኒክ፣ ሀኪም፣ ወይም ሆስፒታል ከሄዱበት ቀን አንስቶ በስድስት (6) ወራት ውስጥ ተመላሽ መጠየቅ አለብዎ። ጥያቄ ለማቅረብ ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የእርስዎን የ HSCSN የእንክብካቤ አስተዳዳሪ ወይም የደምበኛ አገልግሎትን ያግኙ በ (202) 467-2737።

# የቀደመ መመሪያ

## ሌላ ኢንሹራንስ ካለኝ ማድረግ የሚገባኝ

የ HSCSN ተመዝጋቢ ከሆኑና፣ሌላ ኢንሹራንስ ካሎት ወዲያውኑ ይህንን ለእኛ ማሳወቅ አለብዎ። እባክዎ ለደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።

## ለሁለቱም Medicaid እና Medicare ብቁ ከሆንኩ ምን ማድረግ አለብኝ

ሁለቱም Medicare እና Medicaid ካለዎ፣ እባክዎ የ Medicare አቅራቢዎችን እንዲመርጡ ለHSCSN ያሳውቁ። Medicare ካሎት፣ በማዘዣ ለሚሰጡ መድሃኒቶችዎ ለ Medicare Part D መመዝገብ አለብዎ። Medicaid ለጋራ-ከፋዮችዎ ይከፍላል። ለተጨማሪ መረጃ የዚህን መመሪያ መጽሃፍ ገጽ 74 ይመልከቱ።

**የቀደመ መመሪያ (Advance Directive) ማለት ሌሎች ሰዎች የጤና እንክብካቤ ምርጫዎችዎን እንዲያውቁ ለማድረግ የሚፈርሙት የህግ ሰነድ ነው። ጥቅም ላይ የሚውለው ለራስዎ መናገር በማይችሉባቸው ጊዜያት ነው። አንዳንድ ጊዜ በህይወት ዘመን እያለ የሚጠቅም ኑዛዜ ወይም የረጅም ጊዜ የውክልና ስልጣን" በመባል ይታወቃል።**

የቀደመ መመሪያ እርስዎን በመወከል ለእርስዎ የህክምና ምርጫዎችን መወሰን የሚችል ሰውን እንዲመርጡ ያስችልዎታል። የቀደመ መመሪያ በተጨማሪም ፍላጎቶችዎን ለመናገር እስከማይችሉበት ደረጃ ድረስ በጠና ቢታመሙ ምን አይነት ህክምና እንደሚፈልጉ የመግለጽ እድል ይሰጥዎታል።

ስለ የቀደመ መመሪያ ከቤተሰብዎ፣ ከ PCP እና በእንደዚህ አይነት ጉዳዮች ላይ ሊያግዝዎ ከሚችሉ ከሌሎች ሰዎች ጋር መወያየት ጠቃሚ ነው

የቀደመ መመሪያን መሙላትና መፈረም ከፈለጉ፣ በቀጣዩ ቀጠሮዎ ወቅት የእርስዎን PCP እንዲያግዝዎ ይጠይቁ ወይም ለአባላት አገልግሎት በ (202)467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ እና እኛ እናግዝዎታለን።

# ማጭበርበር

ማጭበርበር ከባድ ጉዳይ ነው። ማጭበርበር ምንድን ነው? ማጭበርበር ማለት በእውነተኛው መንገድ ማግኘት የማይቻል የነበረን ጥቅም ወይም ክፍያ ለማግኘት የሃሰት መረጃን መስጠት ወይም እውነታዎችን ማዛባት ማለት ነው። አንድ ተመዝጋቢ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውጪ እየኖረ በዲትሪክቱ ውስጥ እንደሚኖር አድርጎ በሃሰት ከቀረበ ይህ የማጭበርበር ድርጊት ምሳሌ ነው። ላልተሰጡ አገልግሎቶች እና/ወይም አቅርቦቶች ሂሳብ ማስከፈል ደግሞ በአገልግሎት አቅራቢዎች ከሚፈጸሙ የማጭበርበር ተግባራት መካከል አንዱ ምሳሌ ነው።

አንድ የማጭበርበር ድርጊት እንደተፈጸመ ከተጠራጠሩ እባክዎ ያሳውቁን። እራስዎን እንዲገልጹ ወይም ስም እንዲጠቅሱ አያስፈልግም። ማጭበርበር ምን እንደሆነ ለማወቅ ተጨማሪ መረጃ የሚፈልጉ ከሆነ፣የ HSCSN ድረገጽን በ www.hscsnhealthplan.org ይጎብኙ። ማጭበርበርን ሪፖርት ለማድረግ፣ የ HSCSN የቅሬታ፣ ይግባኝ እና አፈጻጸም የስልክ መስመር ጋር በ (202) 495-7582 ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ በ compliance@hschealth.org ወይም የዲሲ የጤና እንክብካቤ የፋይናንስ ማጭበርበር የስልክ መስመር ጋር በ 1-877-632-2873 ይደውሉ።

## የሃኪም (ዶክተር) የክፍያ እቅድ መግለጫ

HSCSN ከ HSCSN ሀኪሞች ጋር ልዩ የገንዘብ ስምምነት ካለው የማወቅ መብት አሎት።

እባክዎ ለዚህ መረጃ ለደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549 ይደውሉ።



# ቅሬታዎች፣አቤቱታዎች፣ እና ፍትሃዊ የክስ መስማት ሂደት

HSCSN እና የዲስትሪክቱ መንግስት ሁለቱም ስለሚያገኙት እንክብካቤ ወይም HSCSN ስለሚያቀርብልዎት አገልግሎቶች ቅሬታዎን ማቅረብ የሚችሉበት መንገዶች አላቸው። አቤቱታዎን የሚያቀርቡበትን መንገድ ከዚህ በታች ከተገለጹት ውስጥ እንዴት ማቅረብ እንዳለብዎ መምረጥ ይችላሉ።

## ቅሬታዎች

- ባጋጠምዎ ነገር ደስተኛ ካልሆኑ አቤቱታ ወይም ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። አቤቱታ ወይም ቅሬታ ሊያቀርቡባቸው የሚችሉ ምክንያቶች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፥
    - በአክብሮት እንዳልተስተናገዱ ከተሰማዎት።
    - ባገኙት የጤና እንክብካቤ አልተደሰቱም።
    - ቀጠሮ ለማግኘት በጣም ብዙ ጊዜ ወሰደብዎት።
- ቅሬታ ለማቅረብ፣ የHSCSN የቅሬታ፣ ይግባኝ እና አፈጻጸም የስልክ መስመር ጋር መደወል ይችላሉ በ (202) 495-7582።
- ቅሬታ ለማቅረብ እርዳታ ከፈለጉ፣ የደምበኛ የእንክብካቤ አገልግሎቶችን ያግኙ በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549።
- በተጨማሪ የእርስዎ ሀኪም የእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ካለ ቅሬታ ሊያቀርብልዎ ይችላሉ።

ያላስደሰቶት ነገር ከተከሰተ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። HSCSN አብዛኛውን ጊዜ በ 90 የካላንደር ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጦታል ነገር ግን ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ጊዜ (ግን በአጠቃላይ 14 ቀናት ያልበለጠ) ሊጠይቅ ይችላል። HSCSN የቅሬታ ደብዳቤዎ እንደደረሰን ለማሳወቅ በሁለት (2) የሥራ ቀናት ውስጥ ደብዳቤ ይልክልዎታል።

HSCSN ጋር ቅሬታ በጽሁፍ ቅሬታ ለማቅረብ፣ ይላኩ ወደ፣

> ATTN፥ የስጋት አስተዳደር
> 1101 Vermont Avenue NW
> Suite 1200
> Washington, DC 20005
> riskmanagement@hschealth.org

## ይግባኝና ፍትሃዊ የክስ መስማት ሂደት

ጥቅሞችዎ ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ እንደተከለከሉ፣ እንደተቀነሱብዎ፣ እንደዘገዩ ወይም እንደተቋረጡ ካመኑ፣ ለHSCSN ይግባኝ ማለት ይችላሉ። ለHSCSN ባቀረቡት ይግባኝ ውሳኔ ካልረኩ፣ የዲሲ አስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ ጋር "ፍትሃዊ ችሎት" መጠየቅ ይችላሉ።

HSCSN ጋር ቅሬታ ለማቅረብ፣ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549.

HSCSN ጋር ቅሬታ በጽሁፍ ቅሬታ ለማቅረብ፣ ይላኩ ወደ፣

> Health Services for Children with Special Needs, Inc.
> ATTN፥ UM-Appeals
> 1101 Vermont Avenue NW, Suite 1200
> Washington, D.C. 20005

የፍትሃዊ ክስ የመስማት ሂደት ጥያቄ ለማቅረብ በሚከተለው አድራሻ ከዲትሪክቱ መንግስት ይደውሉ ወይም ይጻፉ፣

District of Columbia Office of Administrative Hearings
Clerk of the Court
441 4th Street, NW
Suite #450 North
Washington, DC 20001
የስልክ ቁጥር፣ 202-442-9094

ማብቂያ ጊዜዎች፣

- ጎጂ የጥቅማጥቅም ውሳኔ ማስታወቂያ ከተላከበት ቀን ጀምሮ በ60 የካሌንደር ቀናት ዉስጥ ይግባኝ መጠየቅ አለብዎ።
- የHSCSN የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያ ቀን ጀምሮ በ120 የካላንደር ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- የፍትሃዊ የክስ መስማት ሂደት ጥያቄ ወይም ይግባኝ አቅርበው በነበረበት ጊዜ ጥቅሞቹን መቀበልዎን መቀጠል ከፈለጉ የፍትሃዊ የክስ መሰማት ሂደቱን ወይም ክሱን ማቅረብ ያለብዎ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ውስጥ ዘግይቶ በሚደርሰው ቀን ውስጥ ነው:
    - የHSCSN ጎጂ የጥቅማጥቅሞች ዉሳኔ ማስታወቂያ በፖስታ ከተላከበት ቀን ወይም የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያ ጀምሮ በ10 የካላንደር ቀናት ውስጥ ወይም
    - የHSCSN የሚወስደው እርምጃ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን (ወይም፣ በሌላ አነጋገር፣ ጥቅማጥቅሙ የሚቆምበት ቀን)።

የአገልግሎት አቅራቢዎ በጽሁፍ ፈቃድዎን ከሰጧቸው እርስዎን በመወከል የፍትሃዊ የክስ መስማት ሂደት ጥያቄ ወይም ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

## ይግባኞች

ይግባኝዎን ያቀረቡት በስልክ በመደወል ከሆነ HSCSN በስልክ ያቀረቡትን ይግባኝ ወደ ደብዳቤ ይቀይርና እርስዎ እንዲፈርሙበት ደብዳቤዉን ይልክልዎታል። ደብዳቤውን በጥንቃቄ ማንበብዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

ይግባኝዎን ካስገቡበት ቀን ጀምሮ በ 30 የካላንደር ቀናት ውስት በ HSCSN ውሳኔ ይሰጥበታል።

HSCSN መረጃ ለማግኘት ተጨማሪ ጊዜ የሚፈልግ እና ዲስትሪክቱ ይህ ለእርስዎ ተመራጭ መሆኑን ከወሰነ፣ ወይም እርስዎ ወይም የእርስዎ ስልጣን የተሰጠው ተወካይ ተጨማሪ ጊዜ ከጠየቁ፣ HSCSN የይግባኝ ውሳኔ ጊዜን በ 14 ካላንደር ቀናት ሊጨምር ይችላል። HSCSN ስለመራዘሙ የጽሑፍ ማስታወቂያ ሊሰጥዎት ይገባል።

እርስዎ የHSCSN በይግባኝዎ ላይ የሰጠውን ውሳኔ የጽሁፍ ማስታወቂያ በፖስታ ይደርስዎታል።

እርስዎ በHSCSN የይግባኝ ውሳኔ ደስተኛ ካልሆኑ ፍትሃዊ ችሎትን መጠየቅ ይችላሉ።

## የተፋጠነ (አስቸኳይ) ቅሬታዎች እና የይግባኝ መስማት ሂደት

ይግባኝዎ አስቸኳይ መሆኑ ከተወሰነ፣ HSCSN በ 72 ሰዓታት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥዎታል። አንድ ይግባኝ አስቸኳይ ነው የሚባለው መደበኛውን የይግባኝ ስነስርዓት መጠበቅ ለእርስዎ ጎጂ ወይም ስቃይ ከሆነ ነው።

የይግባኝ ጥያቄው ሲመረመር፣ ይግባኙ ወዲያውኑ ሊገኝ ስለሚገባ አገልግሎት የሚመለከት ከሆነ፣ HSCSN በ 24 ሰዓታት ወይም ከጥያቄው ጋር ተስማሚ በሆነ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

**ቅሬታዎች፣ይግባኞች እና ፍትሃዊ የክስ መስማት ችሎት ጥያቄዎች ባቀረቡበት ወቅት የሚኖሩዎ መብቶች**

- ፍትሃዊ የክስ መሰማት ሂደት መብት አሎት። ባለ አንድ ደረጃ ያለው የይግባኝ ሂደት HSCSN ካጠናቀቁ በኋላ፣ የአስተዳደር ችሎት ቢሮ ጋር ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- ጎጂ የጥቅማጥቅም ውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ካለው ቀን ጀምሮ ከ120 የካላንደር ቀናት ሳያልፉ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ አለብዎ።
- የእርስዎን ይግባኝ በተመለከተ HSCSN ማስታወቂያ ካልሰጡት ወይም ጊዜውን ሳይጠብቅ ከሰጡት፣ የይግባኝ ሂደቱ እንደተጠናቀቀ ይቆጠራል እና ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- ይግባኝዎ ወይም የፍትሃዊ የክስ መሰማት ሂደት ጥያቄዎ በሂደት ላይ ባለ ጊዜ የተከለከሉትን ጥቅሞጥቅሞች እየተቀበሉ የመቆየት መብት አለዎት። በፍትሃዊ የክስ መስማት ሂደት ወቅት ጥቅማጥቅሞችዎን እንደያዙ ለመቆየት፣ ፍትሃዊ ችሎትን በተወሰነ ቀናት ውስጥ መጠየቅ አለብዎ - ይህ 10 የካላንደር ቀናት ሊሆን ይችላል።
- በቅሬታዎች እና ይግባኞች ሂደት ውስጥ ከ HSCSN አንድ ሰው እንዲያግዝዎ ያድርጉ።
- እርስዎ ራስዎን ወክለው የመቅረብ፣ በቤተሰብዎ ተንከባካቢዎ፣ በጠበቃዎ፣ ወይም በሌላ ሰው በመወከል የመቅረብ መብት አሎት።
- ላለዎት ለማንኛውም ልዩ የጤና ጥበቃ እንክብካቤ ፍላጎት አቅርቦቶች የማግኘት መብት አሎት።
- የበቂ የ TTY/TTD አቅሞች፣ እና ማየት ለተሳናቸው የአገልግሎቶች መብት አሎት።
- እርስዎ ተገቢ የትርጉም አገልግሎትና አስተርጓሚ የማግኘት መብት አሎት።
- ከቅሬታው፣ ከይግባኙ ወይም ከፍትሃዊ የክስ መስማት ሂደት ጥያቄው ጋር የተያያዙ ሁሉንም ሰነዶች በጠቅላላ የማየት መብት አሎት።

እርስዎ ስለቅሬታው፣ ይግባኙ ወይም ፍትሃዊ የክስ መስማት ሂደት ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት እባክዎ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎትን ጋር ይደውሉ በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549።

## የግላዊነት ተግባራት ማሳወቂያ

ይህ ማስታወቂያ የእርስዎ የሕክምና መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል፣ እና ይህን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልጻል። እባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡ።

**ይህ ማስታወቂያ የእርስዎ የሕክምና መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና እንደሚጋራ ይነግራል።በተጨማሪ ይህን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይነግራል።እባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡ።**

ልዩ ፍላጎቶች ላላቸው ልጆች የጤና አገልግሎቶች፣ Inc. (HSCSN) የጤና መረጃዎን ግላዊ አድርጎ ማቆየት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያውቃል።

የግል መረጃዎን ደህንነቱን ጠብቀን እናቆያለን እና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል በተናገርነው ልክ ብቻ እንጠቀምበታለን።

የግል መረጃዎን በህጉ መሰረት እና በዚህ ማሳወቂያ ውስጥ በተናገርነው መሰረት ብቻ እንጠቀምበታለን። ይህንን ማሳወቂያ በማንኛውም ጊዜ የመለወጥ መብት አለን። ማስታወቂያው በ www.hscsnhealthplan.org. ሊገኝ ይችላል። እርስዎ በማንኛውም ጊዜ ለኮፒው ሊጠይቁ ይችላሉ።

የተለያዩ ህጎች ስለ ጤና መረጃ የተለያዩ ነገሮችን ይላሉ።

- የጤና መረጃ ማለት የእርስዎ ወይም የልጅዎ ጤና እንክብካቤ የሚመለከት መረጃ ነው።
- የግል መረጃ ማለት ለእርስዎ ወይም ለልጅዎ ጥቅማጥቅሞችን ስንሰጥ ያገኘነው የጤና መረጃ እና ማንኛውም ሌላ መረጃ ማለት ነው። ይህ አድራሻዎ እና የማህበራዊ ደህንነት/ዋስትና ቁጥር ሊሆን ይችላል።

ህጉ ይህንን ማስታወቂያ ለእርስዎ መስጠት እንዳለብን ይነግረናል። ስለሚከተለው ይነግሮታል፥

- ስለ እርስዎ እና ልጅዎ የጤና መረጃን ልንጠቀም የምንችልባቸው መንገዶች።
- የእርስዎ መብቶች
- ይህንን መረጃ እንዴት እንደምንጠቀም እና ለሌሎች ሰዎች እንዴት እንደምንናገር በተመለከተ ግዴታዎቻችን።

## የጤና መረጃ

የጤና መረጃን የጤና አገልግሎቶችን ለመስጠት ከእርስዎ ወይም ከሌሎች ልናገኝ እንችላለን። በተጨማሪ ከሚከተሉት መረጃ እናገኛለን፥

- የጤና እንክብካቤ ጠያቂዎች እና ገጠመኞች።
- የህክምና ታሪክ
- የአገልግሎት ጥያቄዎች
- ቅሬታዎች እና ይግባኞች

## የግል መረጃ ግላዊነት እንዴት እንደምንጠብቀው

የእርስዎን የጤና መረጃ እንደሚከተለው እንጠብቃለን፥

- ስለ እርስዎ ወይም ልጅዎ የግል መረጃን ማወቅ ለሚያስፈልጋቸው የ HSCSN ሰዎች ብቻ መስጠት።ይህ ለእርስዎ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን እንድንሰጡት ይረዳናል።
- ሁሉም የግል መረጃን ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ።
- ስለእርስዎ ወይም ልጅዎ መረጃ ከመላካችን በፊት በእያንዳንዱ ጊዜ ፈቃድ መጠየቅ።

ሌሎች ስለ እርስዎ ወይም ልጅዎ የምንሰጣቸውን መረጃ ለማንኛውም ሌላ ሰው መናገር አይፈቀድላቸውም።ህጉ ይህ ነው።

## የጤና መረጃን እንዴት እንደምንጠቀም እና እንደምንለቀው

ህጉ እንደሚለው ለሚከተሉት ነገር ያለ እርስዎ ፈቃድ የጤና መረጃን መጠቀም እንደምንችል ነው፥

- ሕክምና —መረጃን ህክምና ለሚያቀርቡ ሰዎች ልንሰጥ እንችላለን።
    - ሀኪሞች
    - ነርሶች
    - ቴክኒሻኖች
    - ሌሎች ሰራተኞች
    - ሌሎች ግለሰቦች
- ክፍያ —እኛ ስለ ተመዝጋቢ የጤና መረጃን መጠቀም እና ለሌሎች መስጠት እንችላለን የሚከተለውን ለመወሰን፣
    - አገልግሎቱ ወይም እቃው ሽፋን ያለው ስለመሆኑ።
    - እንክብካቤን ለማቀነባበር።
    - አገልግሎቱ በህክምና አስፈላጊ እንደሆነ ለመገምገም።
    - የክፍያ ጥያቄዎችን ለመክፈል ወይም ለመገምገም።
    - ቅሬታዎችን ለመመለስ።
- የጤና እንክብካቤ አሰራሮች —በጤና እንክብካቤ አሰራሮች ለመርዳት የእርስዎን ወይም የልጅዎን የግል መረጃን ልንጠቀም እና ለሌሎች ልንሰጥ እንችላለን። ይህ ሊጨምር የሚችለው፥
    - የጥራት ማሻሻል ተግባራት።
    - ዕውቅና መስጠት
    - ጥያቄዎችን መመለስ
    - ይግባኞች እና የግምገማ ፕሮግራሞች።
    - የጤና ማስታወቂያ
    - የጉዳይ አስተዳደር እና እንክብካቤ።
    - አጠቃላይ የቢሮ ስራዎች
    - አንድ አንድ ጊዜ ለሚከተለው ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፥
        - ኦዲት
        - የፋርማሲ ፕሮግራሞችን እና ክፍያዎችን መገምገም።
        - የሁሉም ወይም የከፊል የ HSC ሥርዓት ሽያጭ፣ ዝውውር፣ ወይም አንድ ላይ መዋሃድንለማገዝ ከሌላ ድርጅት ጋር።

ይህ ዝርዝር መረጃ መሰጠት የሚችልበትን እያንዳንዱን ምክንያት አይጨምርም። እርስዎ የፈቃድ ማግኛ ቅጽን ለመፈረም ይጠየቃሉ እና እርሱም ስለነዚህ ተግባራት መረጃ ይጨምራል።

## ሌሎች የተፈቀዱ ወይም የሚፈለጉ ጥቅሞች

ህጉ ያለ እርስዎ ፈቃድ ለሚከተሉት ምክንያቶች የእርስዎን ወይም የልጅዎን የጤና መረጃን እንድንጠቀም ወይም ለሌሎች እንድንሰጥ ይፈቅድልናል፣

- የጤና እንክብካቤን ለሚቆጣጠሩ የፌዴራል ወይም የስቴት ኤጀንሲዎች ለመታዘዝ።
- እንደ እርስዎ የጤና እንክብካቤ ኢንሹራንስ ሰጪ ከእህት ኩባኒያዎቻችን ጋር የገባናቸውን ቃል ለማሟላት።
- የጤና እቅድ ስፖንሰሮች የእቅድ አስተዳደርን እንዲፈጽሙ ለማድረግ።
- የእርስዎን ግላዊነት ለመጠበቅ ሁሉንም ህጎች ለሚከታተሉ የምርምር ቡድኖች።
- ለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ሌሎች ህጋዊ አካሄዶች ለመገዛት።
- አገልግሎቶችን ለእኛ ለሚያቀርብ ማንኛውም ሰው። እነሱ ሁሉንም መረጃ ደህንነቱ የተጠበቀ እና በአስተማማኝ ሁኔታ እንደሚያቆዩ ማረጋገጥ አለባቸው።
- ስለ ህክምና አማራጮች ወይም ከጤና ጋር የተያያዙ ጥቅማጥቅሞች ወይም አገልግሎቶች ለእርስዎ ለማሳወቅ።
- አንዳንድ ጊዜ፣ ስለ እርስዎ ወይም ልጅዎ የጤና መረጃን ያለ ፍቃድ ለኤጀንሲዎች ለመስጠት በፌዴራል እና ስቴት ሕግ ይፈቀድልናል። ለምሳሌ፥
    - የበደል ወይም ችላ የማለት ተጠቂዎችን ለመጠበቅ።
    - ጤና ወይም ደህንነት ላይ የሚመጡ ከባድ ስጋትን ለማስወገድ።
    - በሽታዎችን ወይም የህክምና ለመከታተል።
- በተጨማሪ እርስዎ የታጠቁ ሃይሎች ተመዝጋቢ ከሆኑ ለወታደራዊ ወይም የቀድሞ ወታደር ባለስልጣናትን ልናሳውቅ እንችላለን።
- መረጃ ልንሰጥ እንችላለን፥
    - ለአስከሬን ገናዦች
    - ለሰራተኞች የጉዳት ካሳ
    - ለብሄራዊ ደህንነት
    - ህግ እንድንሰጥ ለሚያዘን ለማንኛውም ሰው።
- የሰውነት አካል፣ የዓይን፣ ወይም የሕብረ ሕዋሳት ንቅለ ተከላን ለሚያካሂዱ ድርጅቶች ወይም የሰውነት አካል ልገሳ ባንክ የጤና መረጃ እንሰጣለን። ይህ የሰውነት አካል ንቅለ ተከላዎች እና የሰውነት አካል ልገሳዎችን ቀላል ለማድረግ ይረዳል።
- እኛ እርስዎን ወይም ልጅዎን የማይለይ የጤና መረጃን እንድንጠቀም ይፈቀድልናል።
- እርስዎ በጽሁፍ ስምምነትዎን ከሰጡ የጤና መረጃዎን ለቤተሰብዎ አባላት ወይም ጓደኞች ልንሰጥ እንችላለን።

ከጠየቁ፣ ምን ዓይነት መረጃ እንደተለቀቀ እንነግሮታለን። እንዲሁም ማን እንዳገኘው እና ለምን እንደሆነ እንነግሮታለን።

## ሌሎች የጤና መረጃ ጥቅሞች

- ለማንኛውም ምክንያት ስለ እርስዎ ወይም የልጅዎ የጤና መረጃን አንጠቀምም ወይም ለማንም አንናገርም። መረጃን የምንጋራበት ብቸኛው ጊዜ ከላይ ለተዘረዘሩ ምክንያቶች ወይም የእርስዎን ፈቃድ በጽሁፍ ካገኘን ነው።
- እኛ ባለፈ ጊዜ ካገኘነው ማንኛውም የእርስዎ ፈቃድ የተለየ ማግኘት አለብን።
- የጤና መረጃን ለመጠቀም ወይም ለመልቀቅ ፈቃድ ከተሰጠን፣ ፈቃዱ በማንኛውም ጊዜ ሊቆም ይችላል። በጽሁፍ ሊያሳውቁን ይገባል።

- ፈቃዱ ከቆመ፣ ከዚህ በኋላ ስለ እርስዎ ወይም ልጅዎን የሚመለከት መረጃን አንጠቀምም ወይም ለማንም አንሰጥም።
- አስቀድመው ፈቃድ ሰጥተው ከሆነ ማንኛውም ቀድሞ የተደረገ አጠቃቀምን ወይም መለቀቅን ወደ ኋላ ልንመልስ አንችልም።

የHIV ወይም የአደንዛዥ እጽ መጠቀም ላይ የእርስዎን ወይም የልጅዎን መረጃ የሚመለከት የተለዩ ደንቦች አሉ።

- ያንን መረጃ ያለ ልዩ ፎርማ ያለው የጽሁፍ ፈቃድ መስጠት አንችልም።
- ይህ ከላይ ከገለጽናቸው ፈቃድ እና ስምምነት የተለየ ነው።
- ሕጉ የተፈረመ ፈቃድ እና ልዩ የጽሁፍ ፈቃድ ሁለቱንም እንዲኖረን ይገልፃል።

ለ HIV ወይም የአደንዛዥ እጽ መጠቀም መዝገቦች ለየት ያሉ ሕጎች አሉ። እርስዎ ወይም የልጅዎ ህጋዊ ተንከባካቢ ሁሉንም ፈቃዶችን እና ስምምነቶችን መስጠት አለባችሁ።

## የጤና መረጃን የሚመለከቱ መብቶች

እርስዎ፣ ልጅዎ፣ እና የልጅዎ ተንከባካቢ የጤና መረጃቸውን በተመለከተ የሚከተሉት መብቶች አላችሁ።

## የጤና መረጃን የማየት እና ኮፒ የማድረግ መብት

ብቸኛው ልዩ ምክንያት ለሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎች ወይም ሌሎች የተወሰኑ ምክንያቶች ናቸው። የጤና መረጃውን ከማየትዎ እና/ወይም ኮፒ ከማድረግዎ በፊት የጽሁፍ ጥያቄ ለእኛ መላክ ይኖርብዎታል። ለኮፒ ማድረጊያ፣ መላኪያ ወይም ሌሎች ግብዓቶች ዋጋ ክፍያ ሊቆረጥ ይችላል።

## መዝገቡን የመቀየር መብት

የጤና መረጃው ትክክል ካልሆነ፣ መረጃን እንድንቀይር ሊጠይቁን ይችላሉ። መረጃውን እንዲቀይሩ ካልፈቀድንልዎት፣ ለምን እንደሆነ በጽሁፍ እናሳውቆታለን።

## የመረጃ ማውጫዎች ተጠያቂነት መብት

ይህ ስለ እርስዎ ወይም ልጅዎ የህክምና መረጃን የሰጠናቸው ሰዎች ዝርዝር ነው። ይህ የህክምና፣ ክፍያ፣ እና የጤና እንክብካቤ አሰራሮች አካል ያልሆነ ስለ እርስዎ ወይም ልጅዎን የሚመለከት መረጃ ነው። ይህንን ዝርዝር ለማግኘት፥

- ስለዝርዝሩ በጽሁፍ መጠየቅ አለብዎት።
- በምን ዓይነት የጊዜ ቆይታ እንደሚፈልጉ ሊነግሩን ይገባል።
- ከ 6 ዓመታት በፊት በላይ መርዘም የለበትም።
- ከኤፕሪል 14፣ 2003 በፊት የነበሩ ቀናትን ሊጨምር አይችልም።

ዝርዝሩን ከክፍያ ነፃ እንሰጥዎታለን። በተመሳሳይ 12-ወር ጊዜ ውስጥ ከዚህ በፊት ዝርዝሩን የሰጠንዎ ከሆነ ዝርዝሩን ከክፍያ ነፃ አንሰጥዎትም።

በሕግ እንደተገለጸው፣ የተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የግልጽ ማድረግ ተጠያቅነት የመቀበል መብትዎን ለአጭር ጊዜ ልናግድ እንችላለን።

## መገደቦች (ገደቦች) የመጠየቅ መብት

የምንጠቀመው ወይም ለሌላ ሰው የምንሰጠው የጤና መረጃ ላይ ገደብ የመጠየቅ መብት አለዎት። ይህ ስለሚከተሉት መረጃ ያካትታል፥

- ህክምና
- ክፍያ
- የጤና-እንክብካቤ አሰራሮች

በተጨማሪም በእንክብካቤ ወይም ክፍያው ውስጥ ለሚሳተፍ ሰው ስለ እርስዎ ወይም ልጅዎ የምንሰጠው የጤና መረጃ ላይ ገደብ የመጠየቅ መብት አሎት።

የተጠየቀው ገደብ ላይ የመስማማት ግዴታ የለብንም።

### ሚስጥራዊ መልዕክት ልውውጥ መብት

የጤና መረጃን በተመለከተ በተወሰነ ቦታ ወይም በተወሰነ መንገድ እንዲነጋገሩበት የመጠየቅ መብት አሎት። ተገቢ ለሆኑ ሁሉም ጥያቄዎች እንስማማለን።

### የዚህን ማስታወቂያ የወረቀት ኮፒ የማግኘት መብት

በማንኛውም ጊዜ፣ የዚህን ማስታወቂያ የወረቀት ኮፒ የመጠየቅ መብት አሎት።

## ይህ ማስታወቂያ ላይ የሚደረጉ ለውጦች

እኛ እንችላለን፣

- ይህንን ማሰወቂያ መለወጥ
- ስለ ተመዝጋቢው በእጃችን ያለን የህክምና መረጃ በሚመለከት የተለወጠውን ማስታወቂያ ስራ ላይ ማዋል።
- ወደ ፊት ለምንቀበለው ማንኛውም መረጃ መለወጥ።

ያሁኑን ማስታወቂያ ማጠቃለያ የተፈጻሚነት ቀኑ በላይኛው ቀኝ ጥግ ላይ ያለውን ይዘን እናቆያለን። አሁን ሥራ ላይ ያለውን ማስታወቂያ ቅጂ እርስዎ በማንኛውም ጊዜ ማግኘት ይችላሉ።

## ለተጨማሪ መረጃ ወይም ቅሬታን ሪፖርት ለማድረግ

የግላዊ መብት ህግ ተጥሷል ብለው ካመኑ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ። የኛን ቢሮ ማግኘት ወይም የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ ጸሃፊን ማግኘት ይችላሉ።

አቤቱታን ወደ ጸሃፊ ለማቅረብ፥

- ደብዳቤ ይላኩ ወደ 200 Independence Avenue፣ SW፣ Washington፣ D.C. 20201
- 1 (877) 696-6775 ላይ ይደውሉ።

ቅሬታን ወደ ቢሯችን ለማቅረብ፣ ያግኙ፥

- HSCSN ተገዢነት እና ግላዊነት መኮንን Jason Pounds በ (202) 495-7718።
- HSCSN 1101 Vermont Avenue NW፣ Suite 1200፣ Washington፣ D.C. 20005።

አቤቱታን ስላቀረቡ አይቀጡም።

## የHSCSN Medicare Part D ለMedicare እና Medicaid ለሁለቱም ተመዝጋቢዎች ማስታወቂያ

Medicare እና Medicaid በአንድ ጊዜ ካለዎት መድሃኒቶችዎን ከ Medicare ክፍል D ፕሮግራም ያገኛሉ። ይህ የጀመረው በጃንዋሪ 1፣ 2006 ነው።

HSCSN መድሀኒቶችዎን ለሚከተሉት ብቻ ይሸፍናል፥

- ባርቢቱራተስ (Barbiturates)
- ቤንዞዲያኤፒነስ (Benzodiazepines)
- የተወሰኑ ያለ-ማዘዣ የሚሸጡ መድሃኒቶች።

ስለ መድሃኒቶችዎ ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉት፣ እባክዎ የ HSCSN የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ (202) 467-2737 ወይም 1 (866) 937-4549። ስለ Medicare Part D ጥያቄ ካሉት፣ በተጨማሪ Medicare ጋር መደወል ይችላሉ በ 1-800-MEDICARE (1-800-633-4227) ወይም **www.medicare.gov** መጎብኘት ይችላሉ።



# የጤና ጥበቃ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ቢሮ እና ቢል ኦፍ ራይትስ

የጤና ጥበቃ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ፕሮግራም ከMCO የጤና እንክብካቤ በሚያገኙበት ወቅት እርዳታ እና ምክር የሚሰጥ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግስት ፕሮግራም ነው። የጤና ጥበቃ የሕዝብ እንባ ጠባቂ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ሊሰጥ ይቻላል፣

- ማግኘት የሚችሉትን የጤና ጥበቃ መብት እንክብካቤዎች ማብራራት፤
- ስለ ጤና ጥበቃ ላሉዎት ጥያቄዎችና ስጋቶች ምላሽ መስጠት፤
- እንደ MCO ተመዝጋቢ የእርስዎን መብቶች እና ግዴታዎች እንዲረዱ ያግዝዎታል፤
- በሕክምና አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ድጋፍ ይሰጣል፣
- ስለ ጤና ጥበቃ አገልግሎቶችዎ ጥራት የሚመለከቱ ጥያቄዎችና ስጋቶች ምላሽ መስጠት፤
- ከሀኪምዎ ጋር ወይም ከሌላ የጤና ጥበቃ አገልግሎት አቅራቢ ጋር ያጋጠምዎትን ችግር ለመቅረፍ ማገዝ፤
- ከእርስዎ MCO ጋር የሚኖረውን አቤቱታ እና ችግሮችን መቅረፍ ላይ ድጋፍ ይሰጣል፤
- የይግባኝ ሂደት ላይ ድጋፍ ይሰጣል፤ እና
- ለእርስዎ ፍትሃዊ የክስ ችሎት የማቅረብ ጥያቄ ላይ ድጋፍ መስጠት።

የጤና ጥበቃ የሕዝብ እንባ ጠባቂን ለማግኘት፣ እባክዎን በ 202-724-7491 ወይም 1-877-685-6391 (ከክፍያ ነፃ) ይደውሉ።

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ቅሬታዎች፣ ይግባኞችና ፍትሃዊ የክስ መስማት ችሎት ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ አይሰጥም።
የጤና ጥበቃ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ቢሮ እና ቢል ኦፍ ራይትስ የሚገኙበት ቦታ፥

One Judiciary Square
441 4th Street, NW
Suite 250 North
Washington, DC 20001
Phone: (202) 724-7491
ፋክስ፣ (202) 442-6724
ከክፍያ ነጻ ቁጥር፣ 1(877) 685-6391
ኢሜይል፣ **healthcareombudsman@dc.gov**

# ትርጉሞች

| | |
|---|---|
| **የቀደመ መመሪያ** | የቀደመ መመሪያ ማለት እርስዎ በጣም ታመውና ተጎድተው ለራስዎ መናገር በማይችሉበት ወቅት ሌሎች ሰዎች የጤና እንክብካቤ ምርጫዎችዎን እንዲያውቁ ለማድረግ የሚፈርሙት የህግ ሰነድ ነው። |
| **ጠበቃ** | የጤና እንክብካቤና ሌሎች የሚያስፈልግዎትን አገልግሎቶች እንዲያገኙ የሚያግዝዎ ሰው። |
| **ይግባኝ** | ይግባኝ ማለት HSCSN የጠየቁትን የጤና እንክብካቤ ለመከልከል ወይም የተጠቀሙትን አገልግሎት ላይ ክፍያ ለመከልከል የሰጠው ውሳኔ ላይ ሳይስማሙ ሲቀሩ የሚያቀርቡት ልዩ የአቤቱታ ዓይነት ነው። በተጨማሪ እያገኙ ያሉትን አገልግሎቶች ለማቆም በተሰጠ ውሳኔ ላይ ካልተስማሙ እንደዚሁ ዓይነት አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። |
| **ቀጠሮ** | ለጤና ጥበቃ ፍላጎትዎ እርስዎና ሃኪምዎ ለመገናኘት የሚወስኑት ቀን ነው። |
| **የእንክብካቤ አስተዳዳሪ** | ለ HSCSN የሚሰራ፣ በጤና ለመቆየት የሚያስፈልጎትን እንክብካቤና መረጃ እንዲያገኙ የሚያግዝ ሰው ነው። |
| **ምርመራ** | መታየት የሚለውን ይመልከቱ። |
| **ወሊድ መቆጣጠሪያ (Contraception)** | ከወሊድ መቆጣጠሪያ ጋር የተያያዙ አቅርቦቶች |
| **የሚሸፈኑ አገልግሎቶች** | HSCSN የሚከፍልባቸው አቅራቢ የሚሰጣቸው የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች። |
| **ዲቶክስፊኬሽን (Detoxification)** | ከሰውነት ውስጥ እንደ እጾችና አልኮል የመሳሰሉ ጎጂ ነገሮች ነጻ ማድረግ። |
| **እድገት (Development)** | ልጅ የሚያድግበት መንገድ። |
| **የህመም አስተዳደር ፕሮግራም** | እንደ አስም፣ የደም ግፊት ወይም የአእምሮ ህመም የመሳሰሉ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ወይም ልዩ የጤና ፍላጎቶች ያላቸውን ሰዎች የሚያግዝ ፕሮግራም ነው። |
| **ረጅም ጊዜ የሚቆይ የህክምና መሳሪያ (DME)** | ቤትዎ ውስጥ እንዲጠቀሙት ሃኪምዎ የሚጠይቅዎ ወይም የሚነግርዎ ልዩ የህክምና መሳሪያ ነው። |
| **ድንገተኛ እንክብካቤ** | ከባድ፣ ድንገተኛ፣ አንዳንድ ጊዜ ለሕይወት አስጊ ለሆነ ሁኔታ በአፋጣኝ የሚያስፈልግ ህክምና ነው። |
| **ተመዝጋቢ** | በደምበኛ እንክብካቤ አቅራቢ ኔትዎርክ አማካኝነት የጤና እንክብካቤ የሚያገኝ ሰው። |
| **የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ** | ይህ ካርድ እርስዎ የ HSCSN ተመዝጋቢ እንደሆኑ ለሀኪምዎ፣ ሆስፒታሎችዎ፣ መድሃኒት ቤቶች፣ እና ሌሎች እንዲያውቁ የሚያደርግ ነው። |

| | |
|---|---|
| **EPSDT የቀደመ፣ በየጊዜው የሚደረግ የማጣሪያ፣ ምርመራ እና ህክምና ፕሮግራም** | ከልደት እስከ 21 ዕድሜ ለሆኑ ህፃናት የህክምና ምርመራዎች፣ ቼክአፕ፣ የክትትል ህክምና፣ እና የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ህክምና እንዲያገኙ የሚያስችሉ አገልግሎቶች። በተጨማሪ *HealthCheck ፕሮግራም በመባል ይታወቃል።* |
| **ፍትሃዊ የክስ አሰማም ሂደት** | ይግባኝዎን በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ካልረኩ የስቴት ፍትሀዊ ችሎትን ለዲሲ አስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ |
| **የቤተሰብ እቅድ** | የእርግዝና ምርመራ፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ፣ በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራና ህክምና እና የኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራና የምክር አገልግሎቶች የመሰሰሉ አገልግሎቶች። |
| **የቤተሰብና አጠቃላይ ሃኪሞች** | ቤተሰቡን በሙሉ የሚያክም ሃኪም። |
| **ቅሬታ (Grievance)** | በሚያገኙት እንክብካቤ ወይም HSCSN በሚሰጥዎ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ደስተኛ ካልሆኑ፣ ቅሬታ ለማቅረብ የደምበኛ እንክብካቤ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ። |
| **የእጅ መጽሃፍ** | ይህ መጽሃፍ ስለ HSCSN እና አገልግሎቶቻችን መረጃ ይሰጥዎታል። |
| **የHealth Check ፕሮግራም** | EPSDT የሚለውን ይመልከቱ |
| **መስማት የተሳናቸው (Hearing impaired)** | በደንብ የማይሰሙ ከሆነ ወይም ሙሉ በሙሉ መስማት የማይችሉ ከሆነ። |
| **IDEA** | የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ህግ፣ የእድገት ዝግመት እና ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎት ላላቸው ልጆች አገልግሎት የሚሰጥ የፌዴራል ህግ ነው። |
| **ክትባት (Immunization)** | በመርፌ የሚሰጥ ክትባት። |
| **የውስጥ ደዌ ሃኪም** | እድሜያቸው 14 እና ከዚያ በላይ የሆኑ አዋቂዎችና ልጆች ሃኪም። |
| **የአስተርጓሚ አገልግሎቶች** | ቋንቋዎን መናገር ከሚችል ሰው ጋር መነጋገር ሲያስፈልግዎ ወይም ከሃኪምዎ ወይም ከሆስፒታልዎ ጋር ለመነጋገር እገዛ ሲያስፈልግዎ ከእርስዎ HSCSN የሚሰጥ እገዛ። |
| **የሚተዳደር የጤና ጥበቃ ድርጅት (MCO)** | የጤና እንክብካቤና ጤና ነክ አገልገሎቶችን እንዲሰጥዎ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሚከፈለው ድርጅት። |
| **እርግዝና (Maternity)** | አንድ ሴት ከአረገዘችበት ቀን አንስቶ አራስ እስከሆነችበት ድረስ ያለው ጊዜ። |
| **እንክብካቤ ማድረግ** | አንድ ሰው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖ የሚያስበው፣ የሚሰማው እና የሚያደርገው ነገር። |
| **የኔትወርክ አቅራቢዎች** | የአንድ HSCSN አካል የሆኑና የእርስዎን ጤንነት የሚንከባከቡ ሃኪሞች፣ ነርሶች፣ ጥርስ ሃኪሞችና ሌሎች ሰዎች። |

| | |
|---|---|
| **የማይሸፈኑ አገልግሎቶች** | በአቅራቢ ሲሰጥ HSCSN የማይከፍልላቸው የጤና እንክብካቤ። |
| **የጽንስና የማህጸን ሃኪም (OB/GYN)** | የጽንስና/የማህጸን ሃኪም፥ ነፍሰ ጡር የምትሆንበትን ጊዜ ጨምሮ የሴትን ጤና ለመከታተል የሰለጠነ ሃኪም ነው። |
| **ከኔትወርክ ውጪ የሆኑ አቅራቢዎች** | ጤናዎን የሚንከባከቡ ሀኪሞች፣ ነርሶች፣ ጥርስ ሃኪሞችና ሌሎች ሰዎች፣ ነገር ግን የHSCSN አካል **አይደሉም**። |
| **የህጻናት ሀኪም (ፔዲያትሪሺያን)** | የህጻናት ሃኪም። |
| **መድሃኒት ቤት (Pharmacy)** | መድሃኒት የሚወስዱበት በታ። |
| **የሃኪሞ ማነሳሻ እቅድ** | ሀኪምዎ ከ HSCSN ጋር ማንኛውም ልዩ ስምምነት ካለው ይነግሮታል። |
| **የድህረ ወሊድ እንክብካቤ (Postpartum care)** | አንዲት ሴት ልጅ ከወለደች በኋላ የሚደረግላት እንክብካቤ። |
| **የቅድመ ወሊድ እንክብካቤ** | አንዲት ነፍሰ ጡር ሴት በእርግዝናዋ ጊዜ በሙሉ የሚደረግላት እንክብካቤ። |
| **የመድሃኒት ማዘዣ (Prescription)** | ሐኪሙ ለእርስዎ የሚያዘው መድሐኒት፣መድሃኒቱን ለማግኘት ወደ መድሐኒት ቤት ሊወስዱት የሚገባ። |
| **የበሽታ መከላከል የምክር አገልግሎት** | ጤንነትዎ እንደተጠበቀ ወይም ከህመም ወይም ከጉዳት ርቀው እንዲቆዩ እንዲያግዝዎ ከአንድ ሰው ጋር ማውራት ሲፈልጉ። |
| **ተቀዳሚ ህክምና ሰጪ (PCP)** | ሀኪሙ አብዛኛውን ጊዜ እርስዎን ይንከባከባል። |
| **ቅድመ ፈቃድ** | የጤና እንክብካቤ ወይም ህክምና እንዲያገኙ ከ HSCSN የሚሰጥ የጽሁፍ ፈቃድ። |
| **የአገልግሎት ሰጪ ማውጫ** | የ HSCSN አካል የሆኑ አቅራቢዎች ዝርዝር። |
| **አገልግሎት ሰጪዎች (Providers)** | ጤናዎን የሚንከባከቡ ሃኪሞች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሃኪሞችና ሌሎች ሰዎች። |
| **ሪፈራል (Referral)** | ዋና ሃኪምዎ ሌላ ሃኪም ጋር እንዲታዩ የጽሁፍ ማስታወሻ ሲሰጥዎ። |
| **መደበኛ እንክብካቤ** | ከዋና ሃኪምዎ ወይም ዋና ሃኪምዎ እንዲያይዎ የላክዎ ሃኪም በመደበኝነት የሚያገኙት ህክምና። መደበኛ ህክምና ፣ አካላዊ የጤና ምርመራ፣ እንዲሁም እንደ ስኳር፣ አስም እና የደም ግፊት ለመሳሰሉ የጤና ችግሮች በመደበኝነት የሚያገኙትን ህክምና ሊያካትት ይችላል። |
| **መታየት (Screening)** | ጤናማ እንደሆኑ ለማወቅ ሃኪምዎ ወይም ሌላ የጤና አገልግሎት ሰጪ የሚያደርገው ምርመራ። ይህ የመስማት ምርመራ፣ የማየት ምርመራ ወይም ልጅዎ በጤናማ ሁኔታ እያደገ መሆኑን ለማወቅ የሚደረግ ምርመራ ሊሆን ይችላል። |

| | |
|---|---|
| **ራስን ሪፈር የማድረግ (Self-Referral) አገልግሎቶች** | ከዋና ሀኪምዎ የጽሁፍ ማስታወሻ ወይም ሪፈራል ሳያገኙ ማግኘት የሚችሏቸው የተወሰኑ አገልግሎቶች። |
| **አገልግሎቶች (Services)** | ከሃኪምዎ ወይም ከጤና ጥበቃ አቅራቢዎ የሚያገኙት እንክብካቤ። |
| **ልዩ የጤና ጥበቃ ፍላጎቶች** | ህጻናት እና አዋቂዎች ከሚያስፈልጋቸው የጤና እንክብካቤዎች ወይም ሌሎች አገልግሎቶች የተለየ ወይም በበለጠ የሚያስፈልጋቸው ህጻናትና አዋቂዎች። |
| **ልዩ ሞያተኛ** | እንደ የጆሮ፣ የአፍንጫ እና የጉሮሮ ሃኪም ወይም እንደ የእግር ሃኪም ልዩ ህክምና ለመስጠት የሰለጠነ ሃኪም። |
| **ልዩ እንክብካቤ** | ልዩ አይነት የጤና እንክብካቤ እንድትሰጥ በሰለጠነ ሃኪም ወይም ነርስ የሚሰጥ የጤና እንክብካቤ። |
| **የማምከን ህክምና** | ለወደፊት ልጅ መውለድ የማይፈልጉ ከሆነ የሚሰጥ ህክምና። |
| **የትራንስፖርት አገልግሎቶች** | ወደ ቀጠሮዎ ለመሄድ ከ HSCSN የሚያገኙት ዕርዳታ የሚያገኙት የትራንስፖርት አይነት የህክምና ፍላጎትዎ ላይ ይመሰረታል። |
| **ህክምና** | ከሃኪም የሚያገኙት እንክብካቤ። |
| **አስቸኳይ እንክብካቤ** | አሁኑኑ መሆን የሌለበት ነገር ግን በ 24 ሰዓት ውስጥ ማግኘት ያለብዎት ህክምና። |
| **ማየት የተሳነው** | በደንብ ማየት የማይችሉ ወይም ሙሉ በሙሉ ማየት የማይችሉ ከሆነ። |

**ለበለጠ መረጃ www.hscsnhealthplan.org ይጎብኙ።**
**For reasonable accommodations please call (202) 467-2737.**

If you do not speak and/or read English, please call 202-467-2737 between 7:00 a.m. and 5:30 p.m. A representative will assist you. **English.**

Si no habla o lee inglés, llame al 202-467-2737 entre las 7:00 a.m. y las 5:30 p.m. Un representante se complacerá en asistirle. **Spanish.**

የእንግሊዝንኛ ቋንቋ መናገርና ማንበብ የማይችሉ ከሆነ ከጧቱ 7:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 5:30 ባለው ጊዜ በስልክ ቁጥር 202-467-2737 በመደወል እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። **Amharic.**

Nếu bạn không nói và/hoặc đọc tiếng Anh, xin gọi 202-467-2737 từ 7 giờ 00 sáng đến 5 giờ 30 chiều. Sẽ có người đại diện giúp bạn. **Vietnamese.**

如果您不能講和/或不能閱讀英語，請在上午 7:00 到下午 5:30 之間給 (202) 467-2737 打電話，我們會有代表幫助您。**Traditional Chinese.**

영어로 대화를 못하시거나 영어를 읽지 못하시는 경우, 오전 7시 00분에서 오후 5시 30분 사이에 (202) 467-2737번으로 전화해 주시기 바랍니다. 담당 직원이 도와드립니다. **Korean.**

Si vous ne parlez pas ou lisez l'anglais, s'il vous plaît appeller 202-467-2737 entre 7:00 du matin et 5:30 du soir. Un représentant vous aidera. **French.**

Kung hindi ka nagsasalita ng Ingles o hindi marunong magbasa ng Ingles, tumawag sa 202-467-2737 mula 7:00 hanggang 17:30. Tutulungan ka ng isang kinatawan. **Tagalog.**

Если вы не говорите по-английски или не читаете по-английски, звоните по номеру 202-467-2737 с 7:00 до 17:30. Представитель поможет вам. **Russian.**

Se você não fala inglês ou lê inglês, ligue para 202-467-2737 entre as 7:00 e 17:30. Um representante irá ajudá-lo. **Portuguese.**

Se non parli inglese o non leggi inglese, chiama 202-467-2737 dalle 7:00 alle 17:30. Un rappresentante ti aiuterà. **Italian.**

িআপন যিদ ইংরেজী না বেলন বা ইংেরিজ না পেড়ন, 202-467-2737 কল কর 7:00 েথেক 17:30 পযর | একজন প্রিিতিনধ আপনােক সাহাযয েকরব| **Bengali.**

Wenn Sie kein Englisch sprechen oder kein Englisch lesen, rufen Sie die Nummer 202-467-2737 von 7:00 bis 17:30 an. Ein Vertreter wird Ihnen helfen. **German.**

หากคุณไม่พูดภาษาอังกฤษหรือไม่อ่านภาษาอังกฤษโทร 202-467-2737 ตั้งแต่ 7:00 ถึง 17:30 น. ตัวแทนจะช่วยคุณ **Thai.**

英語を話さないか、英語を読まない場合は、7:00〜17:30 に202-467-2737に電話してください。担当者がお手伝いします。**Japanese.**

Ọ bụrụ na ị naghị asụ ma ọ bụ agụ oyibo, biko kpọọ 202-467-2737 ihe dịka oge elekere asaa nke ụtụtụ (7:00 a.m) ruo na elekere ise na ọkara nke mgbede (5:30 p.m). Onye nnọchiteanya ga enyere gị aka. **Igbo**

Tí ó bá jẹ́ pé o kìí sọ pèlú/àbí ka èdè Gẹ̀ẹ́sì, jọ̀wọ́ pe 202-467-2737 láárín aago méje òwúrọ̀ sí márún àbọ̀ ìrọ̀lẹ́ (7am-5:30pm). Aṣojú kan yóò ràn ọ́ lọ́wọ́. **Yoruba**

THE HSC HEALTH CARE SYSTEM

Health Services for Children with Special Needs, Inc.

**1101 Vermont Avenue, NW, 12th Floor**
**Washington, D.C. 20005**

**3400 Martin Luther King Jr. Avenue SE**
**Washington, D.C. 20032**

**(202) 467-2737**
**1 (866) 937-4549 (toll-free)**

DHCF Department of Health Care Finance

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

ይህ ፕሮግራም ወጪው በከፊል የሚሸፈነው በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ
መንግስት የጤና ጥበቃ ፋይናንስ መምሪያ ነው።
HSCSN አግባብነት ያላቸውን የፌዴራል ሲቪል ሕጎችን ያከብራል እና በዘር፣ ቀለም፣
የብሄራዊ ምንጭ፣ ዕድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት ወይም ጾታ መሰረት አድልዎ አያደርግም።